# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

## የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የመንገዶች አጠባበቅ እና ጥገናን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ታህሳስ 2004 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ


**መግቢያ ........ 1**

የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን አመሠራረት........ 1
ባለስልጣኑ የተቋቋመበት ዓላማ ........ 2
የባለስልጣኑ ሥልጣንና ተግባር ........ 2
የባለስልጣኑ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል ........ 3
የባለሥልጣኑ ፋይናንስ ምንጭ ........ 4

**የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ ........ 5**

**የክዋኔ ኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ ........ 5**

**ለክዋኔ ኦዲት የተለየው የኦዲት አካባቢ (AUDIT AREA) ........ 6**

**የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች (AUDIT ISSUES)........ 6**

**የኦዲት መመዘኛ መስፈርት........ 7**

**የመንገድ ጥገና የሥራ ሒደት መግለጫ (PROCESS DESCRIPTION). ........ 8**

ሀ. ጥገና የሚደረግላቸው መንገዶችን የመለየት፤ ........ 8
ለ. ጥገና እንዲደረግላቸው ኮንትራት የመስጠት፤ ........ 8
ሐ. የመንገድ ጥገናው ተግባር በኮንትራቱ መሠረት መከናወኑን ክትትል ማድረግ፤ ........ 8
መ. የጥገና ሥራው ከተጠናቀቀ በኃላ ርክክብ ማድረግ እና መንገዱን መጠበቅ ........ 9
ለመንገዶች ጥገና የሚያገለግለው መመሪያ ወቅታዊ መሆኑን እና ስለመመሪያው አጠቃቀም ግንዛቤ መስጠቱን በተመለከተ..... 10
በባለስልጣኑ የሚተዳደሩ መንገዶች ታሪክ (ROAD HISTORY) በተመለከተ ........ 10
የመንገድ ጥገና እቅድ ዝግጅትን በተመለከተ........ 11
ለመንገድ ጥገና ተግባር የሚውል ፋይናንስ አሰባሰብን በተመለከተ ........ 12
ለመንገዶቹ ወጥ እና ተከታታይነት ያለው ጥበቃ እና ጥገና የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ ........ 13
ከሚመለከታቸው በባለድርሻ አካላት ጋር የመንገድ ጥገና ክንውን ምክክርን በተመለከተ ........ 16
ለመንገድ ጥገና የሚውሉ ግብዓቶችን የጥራት ደረጃ ማረጋገጥን በተመለከተ ........ 18

**ፎቶ 8፤ በቡሬ ስክሽን በመስክ ስራው ላይ አማካሪው ድርጅት ሳይኖር በዲስትሪክቱ ምህንድስና መምሪያ በኩል ለመንገድ ጥገና ስራው እየተጫነ ያለው ሳር ያለበት የመንገድ ጥገና ግብዓት የተያዘበት ሁኔታ ........ 19**

የመንገድ ጥገና ሥራዎች በሰው ኃይል እና በአነስተኛ የእጅ መሣሪያዎች ማከናወንን በተመለከተ........ 19
ለሚከሰቱ የጥገና መጓተት እና ጥራት ጉድለት ተጠያቂነትን በተመለከተ ........ 22
ከተፈቀደው ክብደት በላይ የጫኑ ሹፌሮች የተቀጡበት የመረጃ አያያዝን በተመለከተ........ 23
የከባድ ተሸከርካሪዎች ክብደት ቁጥጥር የሚያደርጉ ባለሙያዎች የስነምግባር ደንብን በተመለከተ ........ 24
ከተፈቀደው ክብደት በላይ ጭነው በሚንቀሳቀሱ ተሸከርካሪዎች ላይ ተመጣጣኝ ቅጣት የሚጣል ስለመሆኑ........ 24
ለአሽከርካሪዎችና ለሚመለከታቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የመንገድ አያያዝ እና አጠቃቀም ዙሪያ ግንዛቤ መስጠትን በተመለከተ ........ 25
በመንገድ ጥገና ዘርፍ ሊሰጥ የሚገባ ስልጠናን በተመለከተ ........ 26
የመንገድ ጥገና የአፈፃፀም ጥራት አመላካቾችን (PERFORMANCE INDICATORS)ተግባራዊ ማድረግን በተመለከተ........ 27
የመንገድ ጠርዝ/ትከሻ (ROAD SHOULDER) ደህንነት መጠበቅን በተመለከተ........ 28
በመንገድ ጥገና ሥራዎች ላይ ወጥነትና ተከታታይነት ያለው የጥራት ቁጥጥር ኦዲት መደረጉን በተመለከተ ........ 29
መንገዶች ሊሰጡ የሚጠበቅባቸውን ወቅታዊ አገልግሎት ባገናዘበ መልኩ የመንገዶች ጥገና የሚከናወን መሆኑን በተመለከተ ... 30
የመንገድ ጥገና ከመከናወኑ በፊት የአካባቢ እና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ መደረጉን በተመለከተ ........ 31

**መደምደሚያ ........ 33**

**አባሪዎች ........................................................................................................ I**

የአዲት መመዘኛዎች ........................................................................................................ I
የመንገድ አውታር ዝርጋታ መጠን፤ ........................................................................................ IV

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. ዘመናዊ የመንገድ ግንባታ በኢትዮጵያ የተጀመረው በአፄ ሚኒልክ ዘመነ መንግስት እንደሆነ እና የመንገድ ትራንስፖርትን ለማስፋፋት ንጉሡ ጠንካራ ፍላጎት ስለነበራቸው ከአዲስ አበባ እስከ አዲስ ዓለም ያለውን እና በሀገር ደረጃ የመጀመሪያ የተባለለትን የ60 ኪሎ ሜትር ዘመናዊ መንገድ በ1895 ዓ.ም. ማሠራታቸውን፤ በተለይም ተሽከርካሪዎች ለመጀመሪያ ጊዜ አዲስ አበባ በገቡበት በ1900 መግቢያ ላይ የመንገዶች መስፋፋት አስፈላጊነት ይበልጥ እየታወቀ መምጣቱን፤ ጣሊያን ሀገራችንን በወረረበት ከ1928 እስከ 1933 ባሉት አምስት አመታት ውስጥ ዘመናዊ መንገዶች በተሻለ ሁኔታ መሠራት መጀመራቸውን እና እስከ 5000 ኪ/ሜ የሚደርስ መንገድ እና ጥርጊያ ጎዳናዎችን በዚህ ወቅት ሊሠሩ እንደቻሉ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

## የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን አመሠራረት

2. በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን በመባል የሚታወቀው መ/ቤት የሀገሪቱ አውራ መንገዶችን እንዲያሻሽልና እንዲጠብቅ ታስቦ ከ60 ዓመታት በፊት ጥር 18 ቀን 1943 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 115/43 የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግስት የአውራ ጎዳና ባለሥልጣን በሚል ስያሜ የተቋቋመ ሲሆን፣ ከዚያ በመቀጠል አደረጃጀቱ እና ተጠሪነቱ እየተለዋወጠ እስከ 1983 ዓ.ም ቆይቷል፡፡ በ1983 ዓ.ም በወጣው ልዩ ድንጋጌ ቁጥር 26/1983 የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ተብሎ እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡ በመቀጠልም በአዋጅ ቁጥር 63/1985 እንደገና እንዲቋቋም የተደረገ ሲሆን፣ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሳዊ ሪፑብሊክ ከተመሠረተ በኃላ በአዋጅ ቁጥር 80/ 1989 የስያሜ ለውጥ ሳያደርግ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዲሆን ተደርጎ እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡ ከዚህም በመቀጠል የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ አስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀት ለማሻሻል በወጣ አዋጅ ቁጥር 247/2003 መሠረት ተጠሪነቱ ለትራንስፖርት ሚኒስቴር እንዲሆን ተደንግጓል ፡፡በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ያጠናውን መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት መሠረት በማድረግ አደረጃጀቱን የቀየረ ሲሆን፣ በዚህም መሠረት

ተቆጣጣሪ (regulatory) አካል እና የመንገድ ግንባታና ጥገና የሚያከናውነው (operational) አካል እንዲለያዩ ተደርጎ ተደራጅቷል፡፡

3. የአገሪቱን የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ልማት ለማፋጠን መንገዶች ካላቸው የማይተካ ሚና አኳያ በአለፉት ሁለት አስርት ዓመታት የማስፋፋት ተግባር በሰፊው የተከናወነ ሲሆን፣ ባለፉት አሥራ ሶስት ዓመታት ከ1989-2002 ዓ.ም ወይም እ.ኤ.አ(1997-2010) የመንገድ አውታር (network) በከፍተኛ ሁኔታ በመስፋፋት ላይ ይገኛል፡፡ በአጠቃላይ የመንገድ አውታሩ (network) በእያአንዳንዱ ዓመት 4.2 % ያደገ ሲሆን፣ የማህበረሰብ መንገድ (community road ) ሳያካትት በፌዴራል እና በክልል መንግስታት የሚተዳደረው መንገድ አውታር በእነዚህ አሥራ ሶስት ዓመታት 48793 ኪ.ሜ ጨምሯል፡፡ ይህንንም ለማስፈፀም ከመንግስት፣ ከብድር እና ከእርዳታ የተገኘ ብር 60.4 ቢሊዮን ወጪ ተደርጓል፡፡

## ባለስልጣኑ የተቋቋመበት ዓላማ

4. በአዋጅ ቁጥር 47/2003 መሠረት ባለስልጣኑ የተቋቋመው መንገዶችን ለማልማትና ለማስተዳደር፤ የመንገድ አውታር በተቀናጀ መልኩ የሚያድግበትን አመቺ ሁኔታ ለመፍጠር እና የመንገዶችን ሥራ የደረጃ ወጥነትን የማረጋገጥ ተግባራትን ለማከናወን ነው፡፡

## የባለስልጣኑ ሥልጣንና ተግባር

5. በአዋጅ ቁጥር 47/2003 መሠረት ባለስልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ተሰጥተውታል፡፡

- መንገዶችን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችንና ሕጎችን ያመነጫል፤
- የመንገዶችን አመደደብ መመሪያ ያወጣል፤ብሔራዊ የመንገድ አውታርንና የመንገዶችን ደረጃ ይመድባል፡ ይሰይማል፤ የመንገዶችን የዲዛይን ደረጃ ያወጣል፤
- የአገሪቱን የመንገድ አውታር አስመልክቶ የተቀናጀ ዕቅድ ያወጣል፤ለሚመለከታቸው አካለት ያሰራጫል፤
- የአጭርና የረጅም ጊዜ የመንገድ ልማት ዕቅዶችንና ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል፡ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
- ለመንገድ ሥራ የሚያስፈልጉ ዲዛይኖችንና የፊዚቢሊቲ፤ የአካባቢና ተያያዥነት ያላቸውን ጥናቶች ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤
- የመንገድ ሥራዎች እንዲከናወኑ ያስደርጋል፤ ድንገተኛ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በራሱ ኃይል የመንገድ ሥራዎችን ያከናውናል፤
- የሥራ እና የአማካሪዎች አገልግሎት ውሎችን ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ይዋዋላል፤ ሥራዎችን በየውላቸው መሠረት የሚከናወኑ

መሆናቸውን ለማረጋገጥ በበላይነት ይቆጣጠራል ወይም በሌለ አካል ቁጥጥር እንዲካሄድ ያደርጋል፤

- ❖ አግባብነት ያላቸው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ መንግስት የግዢ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የመንገዶችን ዲዛይን የሚሰሩ ወይም የቁጥጥር እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን የሚሰጡ አማካሪዎችን እንዲሁም በመንገድ ስራዎች ላይ የሚሰማሩ ሥራ ተቋራጮች የሚመረጡበትን ዘዴዎች ይወስናል፤
- ❖ የመንገድ ሥራዎችን በሀገር ውስጥ ወይንም በዓለም አቀፍ ጨረታ የሚከናወንበትን አማራጭ ይወስናል፤
- ❖ የትራፊክ መቆጣጠሪያ ምልክቶች እንዲዘጋጁ እና በመንገዶች ላይ እንዲኖሩ ያደርጋል፤
- ❖ የተሽከርካሪ ክብደት ደንቦችን በመንገድ ላይ ያስከብራል፤
- ❖ ከክልል የመንገድ ኤጀንሲዎችና አግባብነት ካላቸው ሌሎች አካላት ሲጠየቅ የምክር እና የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤
- ❖ መንገዶችን በሚመለከት ጥናትና ምርምር ያካሂዳል ወይም እንዲካሄድ ያደርጋል፤ የተገኙ ጠቃሚ ውጤቶችንም በሥራ ላይ የሚውሉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
- ❖ ለመንገድ ልማት የሚያስፈልገውን የሰው ሀይል እንደ አስፈላጊነቱ ያሰለጥናል፤
- ❖ የመንገድ ስራዎች በሚካሄዱበት ወቅት ለአካባቢ ጥበቃ የሚያስፈልጉትን ጥንቃቄዎች ያደርጋል፤
- ❖ በክፍያ የሚያገለግሉ መንገዶችን ይወስናል፤ ከተጠቃሚዎች የሚሰበሰብ የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፤ለመንገዶች ፈንድ ገቢ ያደርጋል፤
- ❖ የንብረት ባለቤት ይሆናል ፤ ውል ይዋዋላል ፤ በስሙ ይከሳል ፤ ይከሰሳል፤ሥልጣንና ተግባሩን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራቶችን ያከናውናል፡፡

## የባለስልጣኑ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል

6. በባለሥልጣኑ በተጠናው የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት መሠረት መንገዶችን በባለቤትነት ይዞ በማስተዳደር የተቆጣጣሪነቱን ተግባር የማከናውን እና የመንገድ ግንባታ እና ጥገናውን ሥራ የማከናውኑ ተግባር ለየብቻ ተለያይተው እንዲከናወኑ የተደረገ ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት የባለሥልጣኑ አደረጃጀት እንዲቀየር ተደርጓል፡፡ በዚህ አዲስ አደረጃጀት የኦፐሬሽን ዋና መምሪያ በሥሩ የሚገኙ የመንገድ ጥገና ጽ/ቤቶች እና የራስ ኃይል ኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶችን መሣሪያዎችና እና ሠራተኞችን ይዞ የመንግስት የስራ ተቋራጭ ተቋም ሆኖ ከኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን የወጣ ሲሆን፣ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን በሬጉላቶሪ ተቋምነት የፌደራል የመንገድ አውታርን ማስተዳደር፤ የመንገድ ፕሮጀክቶች ዲዛይን ማካሄድ እና የመንገድ ግንባታ ኮንትራቶችን ማስተዳደር ላይ አተኩሮ በዘርፉ ጥሩ ልምዶች እንዲዳብሩ የሚያደርግ ተግባራትን እንዲያከናውን ተደርጎ ተዋቅሯል፡፡

7. በዚሁ መሠረት የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 247/2003 የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት እና ዓላማውን ከግብ ለማድረስ በቦርድ እንዲመራ ተደርጎ የተዋቀረ ሲሆን፣ አንድ ዋና ዳይሬክተር በዋና ዳይሬክተሩ ስር የባለስልጣኑን አብይ ተግባር የሚያስፈጽሙ ሦስት ምክትል ዳይሬክተር ጄኔራሎች፤ በእነዚህ ሦስት ምክትል ዳይሬክተር ጄኔራሎች ስር ደግሞ አሥራ አንድ ዳይሬክተሮቶች እንዲሁም በዋና ዳይሬክተሩ ስር አራት ድጋፍ ሰጪ ዳይሬክተሮቶች እንዲኖሩት ተደርጎ ተዋቅሯል ፡፡

8. ለእነዚህ የሥራ ክፍሎች የተመደበው የሰው ኃይል ቋሚ ሠራተኛ 1410 (56.8%) ኮንትራት ሠራተኛ 1072 (43.2%) በድምሩ 2482 ሠራተኛ ያለው ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው 436፣ የኮሌጅ ዲፐሎማ ያላቸው 195፣ በቴክኒክና ሙያ የተመረቁ 121፤ 12ኛ ክፍል እና ከዚያ በታች 1730 ያላቸው ናቸው፡፡

## የባለሥልጣኑ ፋይናንስ ምንጭ

9. በባለሥልጣን መ/ቤቱ ማቋቋሚያ አዋጅ ላይ ለመንገድ ጥገና ሥራዎች ወጪ መሸፈኛ የሚሆን ገንዘብ ከመንግስት እና ከመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት ይመደብለታል በሚል የተቀመጠ ቢሆንም ባለፉት ሶስት ተከታታይ የበጀት ዓመታት (ከ2000 እስከ 2002) ከመንግሥት የተመደበ በጀት እንደሌለ ለማወቅ ተችሏል፡፡ የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት ከ2000 እስከ 2002 ባሉት የሶስት የበጀት ዓመታት እንደ ቅደም ተከተሉ ብር 1.0፤ 1.1 እና 1.1 ቢሊየን ለመንገድ ጥገና ተግባር እንዲውል ለባለሥልጣኑ ለማስተላለፍ ያቀደ መሆኑን ያሳወቀ ቢሆንም በእነዚህ ሶስት ተከታታይ የበጀት ዓመታት ለማስተላለፍ በዕቅድ ከያዘው ውስጥ በቅደም ተከተሉ መሠረት ብር 0.804 (79%)፣ 0.64 (57%) እና 0.97 (89%) ቢሊየን ያህሉን ብቻ ለመንገድ ጥገና ተግባር እንዲውል ለባለሥልጣኑ ያስተላለፈው መሆኑን ከፈንድ ጽ/ቤት ከተገኘ መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

10. በሌላ በኩል ደግሞ ከባለሥልጣኑ በተገኘ መረጃ መሠረት ለመንገድ ጥገና ተግባር እንዲውል ከ2000-2002 በጀት ዓመታት ከመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት የተመደበ በጀት እንደ ቅደም ተከተሉ ብር 0.89፣ 0.60 እና 0.83 ቢሊየን መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በእነዚህ በጀት ዓመታት ሥራ ላይ የዋለው በጀት ሲታይ እንደ ቅደም ተከተሉ ብር 0.73 ብር 0.65 እና ብር 0.85 ቢሊየን ሲሆን፣ በዚህ መሠረት በ2000 በጀት ዓመት ብር 0.17 ቢሊየን ሥራ ላይ ያልዋለ፤ በ2001 በጀት

ዓመት ብር 0.051 እንዲሁም በ2002 በጀት ዓመት ብር 0.02 ቢሊየን ከተመደበው በጀት በላይ ለመንገድ ጥገና ተግባር ሥራ የዋለ መሆኑን ታውቅል፡፡

## የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ

11. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን የመንገድ ጥገና ሥራ በቁጠባ፣ በብቃት እና በስኬታማነት ለማከናወን የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን ለመገምገም ሲሆን፣ በዚህ ዙሪያ ችግሮች ካሉ በመለየት ችግሮቹን ለማቃለል የሚረዱ የመፍትሄ ሃሳቦችን ለማቅረብ ነው፡፡

## የክዋኔ ኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

12. ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ሲሆን፣ ዝርዝር ኦዲቱ የሚሸፍነው ከ2000 እስከ 2002 በጀት ዓመታት ድረስ ያለውን የባለሥልጣኑን የሥራ ክንውን ነው፡፡ ባለሥልጣኑ ያሉት አሥር ዲስትሪክቶች፤ በአለፉት ሶስት አመታት የመንገድ ጥገና ካከናወኑ 12 ኮንትራክቶሮች መካከል አራት፣ ከ12 አማካሪ ድርጅቶች መካከል ደግሞ ሁለት መላክ በዝርዝር ኦዲቱ እንዲታዩ ተደርጓል፡፡
13. የባለሥልጣኑን ከ2000 እስከ 2002 በጀት ዓመታት ያሉትን የሥራ ክንውኖች የሚያሳዩ ዕቅዶች እና የዕቅድ ክንውኖች እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች በመከለስ፤ በዝርዝር ኦዲት ለማየት በሶስት የባለሥልጣኑ ዲስትሪክቶች ማለትም በደብረማርቆስ፤ በጎንደር እና በድሬዳዋ በናሙና የተመረጡ የመንገድ ጥገና ፕሮጀክቶችን የሚገኙበት ቦታ ድረስ በመሄድ እና የሚሠራውን የጥገና ሥራ በመመልከት፤ ዋነኛ ባለድርሻ ከሆኑ እና በአለፉት ሶስት አመታት የመንገድ ጥገና ካከናወኑ ተቋራጮች እና አማካሪዎች መካከል ለአራት ተቋራጮች እና ለሁለት አማካሪዎች የሥራ ኃላፊዎች ቃለ መጠይቅ በማቅረብ እና ያቀረቡትን መረጃዎችን በመከለስ ለኦዲቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተሞክሯል፡፡
14. በአካል ካልታዩ የባለሥልጣኑ ሰባት ዲስትሪክቶች መካከል አንዱ ብቻ ለተላከለት መጠይቅ የሰጠ ሲሆን፣ ከመንገድ ተቋራጮች እና ከአማካሪዎች የተፈለገውን ያህል መረጃ ለማግኘት አልተቻለም፡፡ ሆኖም በአጠቃላይ የተለያዩ የኦዲት ዘዴዎችን በመጠቀም የተሰበሰቡትን መረጃዎች በመተንተን እና በማጠናቀር በመጨረሻም ማብራሪያ ለሚያስፈልጋቸው ነጥቦች ለሚመለከታቸው

የባለሥልጣኑ የሥራ ኃላፊዎች ቃለ መጠይቅ ማቅረብ ለኦዲቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች የማጠናቀር ሥራ ተሠርቷል፡፡

## ለክዋኔ ኦዲት የተለየው የኦዲት አካባቢ (AUDIT AREA)

15. በመንገድ ጥገና ዙሪያ እየታዩ ያሉትን እና የተለዩትን ችግሮች በማገናዘብ የኦዲት ቡድኑ "በኢትዮጵያ መንገዶቾ ባለሥልጣን የሚከናወኑ የመንገድ ጥገና ተግባራት በቁጠባ (economicaly)፣ በብቃት (efficiently) እና በስኬታማነት (effectivelly) እየተከናወኑ መሆኑን መገምገም" የሚል የኦዲት አካባቢ ለይቶ ዝርዝር የክዋኔ ኦዲቱን አከናውኗል፡፡

## የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች (AUDIT ISSUES)

16. ከላይ በተለየውም የኦዲት አካባቢ ስር ሶስት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) የተለዩ ሲሆን፣ በመጀመሪያው የኦዲት አቅጣጫ ሥር ሁለት ንዑስ የኦዲት አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል፤ እነሱም

1 በባለሥልጣኑ የሚከናወኑ የመንገድ ጥገና ተግባራት በቁጠባ (economicaly) እና በብቃት (efficiently) እየተከናወኑ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡

i. የመንገድ ጥገና ሥራን ለማከናወን አግባብነት ያለው የአሠራር ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን ማረጋገጥ

ii. በሚያከናውነው የመንገድ ጥገና ዙሪያ ከሚመለከታቸው የውስጥ እና የውጭ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እና ቁጠባን መሠረት በማድረግ በብቃት እየተሠራ መሆኑን መገምገም፡፡

2 በባለሥልጣኑ የሚከናወኑ የመንገድ ጥገና ሥራዎች የጥራት ደረጃቸውን ጠብቀው ስኬታማ (effective) በሆነ ሁኔታ የሚከናወኑ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡

3 ባለሥልጣኑ የመንገድ ጥገና በሚያከናውንበት ወቅት በአካባቢ ላይ የሚያደርሰውን ተፅእኖ ለመቀነስ ተገቢ እርምጃ የሚወስድ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡

የሚሉ ናቸው፡፡

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

17. ለዝርዝር ኦዲቱ በተለየው የኦዲት አካባቢ ስር ለተቀመጡት የኦዲት ጭብጦች (Audit Issues) 21 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ እነዚህን የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ለማዘጋጀት መሠረት የሆኑት ባለሥልጣኑ የተቋቋመበት አዋጅ፤ የባለስልጣኑ የሥራ መመሪያና ደንቦች እንዲሁም በባለስልጣኑ የተጠናው መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት እና መልካም ተሞክሮዎች ናቸው፡፡ የተዘጋጁት የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ከዚህ ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል (አባሪ 1 ተያይዟል)፡፡

## የመንገድ ጥገና የሥራ ሒደት መግለጫ (Process Description).

### ሀ. ጥገና የሚደረግላቸው መንገዶችን የመለየት፤

18. በየዲስትሪክቱ የሚገኙ የዲስትሪክት ምህንድስና ክፍሎች በቀጠናቸው ያሉ የሚያስተዳድሩአቸውን መንገዶች በዓመት አንዴ በመቃኘት እና ክትትል በማድረግ የመንገዶቹን ይዘት እና ሁኔታ ከኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ፤ ከትራፊክ ፍሰት እና የመንገዶቹን የብልሽት መጠን ወዘተ. በማጥናት ጥገና የሚያስፈልጋቸውን የመለየት እና ምን አይነት (የመደበኛ፤ የወቅታዊ እና የተርም) ጥገና እንደሚያስፈልጋቸው እና ለጥገና የሚያስፈልጋቸውን የገንዘብ ግምት በማስቀመጥ ለባለስልጣኑ የመንገዶች ልማት አስተዳደር ክፍል እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡

19. የቀረቡትን መረጃዎች መሠረት በማድረግ የትኞቹ ቅድሚያ ይሰጣቸው የሚለው በባለስልጣኑ የመንገዶች ልማት አስተዳደር ክፍል ውሳኔ ከተሰጠበት እና ጥገና የሚደረግላቸው መንገዶች ከተለዩ በኋላ ለጥገና ሥራው ማስፈፀሚያ የሚሆን በጀት እንዲመደብ የመንገዶች ፈንድ ጽ/ቤትን ይጠይቃል፡፡

### ለ. ጥገና እንዲደረግላቸው ኮንትራት የመስጠት፤

20. በባለስልጣኑ የቀረበው የበጀት ጥያቄ በመንገዶች ፈንድ ጽ/ቤት ተቀባይነት ሲያገኝ የመንገዱ ጥገና ሥራ ለተቋራጮች በጨረታና በገበያ ዋጋ በመደራደር ወይም እንደአስፈላጊነቱ በራስ ኃይል ለሚከናወን ሥራ በትእዛዝ የሚከናወንበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡ የሚሠሩት የጥገና ሥራዎች በጥራት መሠራታቸውን የሚቆጣጠር አማካሪ ድርጅት የሚያስፈልግ ሆኖ ሲገኝ በባለስልጣኑ በኩል በተመሳሳይ በጨረታና በገበያ ዋጋ በመደራደር ይቀጠራል፡፡ የጥገና ሥራውን ለመሥራት እና የጥራት ቁጥጥር የማድረጉን ተግባር ለማከናወን ተቀባይነት ያገኙት የሥራ ተቋራጭ እና አማካሪ ድርጅቶች ሥራውን ከመጀመራቸው በፊት የሥራ ውል ከባለሥልጣኑ ጋር እንዲፈርሙ ይደረጋል፡፡

### ሐ. የመንገድ ጥገናው ተግባር በኮንትራቱ መሠረት መከናወኑን ክትትል ማድረግ፤

21. በኮንትራክተሩ በኩል የመንገድ ጥገና ሥራውን ለማከናወን ሊተገበር የሚችል የሥራ እቅድ መዘጋጀቱን፤ በመቀጠልም ለመንገድ ጥገናው ሥራ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ለመደልደል የሚረዳ ቀመር በቅድሚያ ተዘጋጅቶ የግብአቶች ድልድል

መከናወኑን፤ የግብዓቶች ድልድል በቂ ካልሆነ ኮንትራክተሩ የማቴሪያል እና የመሳሪያዎች ግዥ/ኪራይ/ ስለመፈጸሙ፤ በቂ የሰው ኃይልም ስለመቀጠሩ በአማካሪ ድርጅቱ ተረጋገጦ ለባለሥልጣኑ ሪፖርተ ከተደረገ በኋላ ለመንገድ ግንባታ በኮንትራክተሩ የተዘጋጁ ቁሳቁሶች እና የሰው ኃይሉ ወደ ሥራ ቦታ ያጓጓዛሉ፡፡

22. በኮንትራክተሩ የሚቀርቡ ለመንገድ ጥገና የሚያገለግሉ ግብአቶች (materials) ጥራት በአማካሪ ድርጅቱ ከተረጋገጠ በኋላ እየተመረቱ ወደ ሥራ ቦታዎች እንዲጓጓዙ ይደረጋል፡፡ በመቀጠልም በአማካሪ ድርጅቱ በኩል የመንገድ ጥገና ጥራት በእያንዳንዱ ሥራና ግብአት ላይ ክትትል እየተደረገ ኮንትራክተሩ የመንገድ ጥገና ፊዚካል ሥራዎችን ያከናውናል፡፡ የተሠሩትን የመንገድ ጥገና ሥስራዎች መረጃ የያዘ ወርሐዊ የሥራ ክንውን የሚያሳይ ሪፖርት እና የክፍያ መጠየቂያ ተዘጋጅቶ ለአማካሪ ድርጅቱ ይቀርባል፤ የባለሥልጣኑ ተወካይ ማለትም አማካሪው በክፍያ መጠየቂያው ላይ ስለትክክለኛነቱ ከፈረመ በኋላ በፋክስ፣ መረጃ መረብ (internet) ለባለሥልጣኑ በመላክ ክፍያ እንዲፈጸም ይደረጋል፡፡

## መ. የጥገና ሥራው ከተጠናቀቀ በኃላ ርክክብ ማድረግ እና መንገዱን መጠበቅ

23. በመጨረሻም በኮንትራቱ መሠረት የጥራት ደረጃውን ጠብቆ የተጠገነው መንገድ ባለሥልጣኑ በኮንትራት ስምምነቱ ላይ በተቀመጠው ስምምነት መሠረት በመረከብ እንዲያስተዳድር ይደረጋል፡፡

# ክፍል ሁለት

# የኦዲት ግኝት

## ለመንገዶች ጥገና የሚያገለግለው መመሪያ ወቅታዊ መሆኑን እና ስለመመሪያው አጠቃቀም ግንዛቤ መሰጠቱን በተመለከተ

24. ለመንገዶች ጥገና የሚያገለግለው መመሪያ በየጊዜው ያለውን ወቅታዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ሊሻሻል እና ይህን መመሪያ በተመለከተ የማስተዋወቅ ተግባር ሊከናወን ይገባል::

25. ለመንገዶች ጥገና የተዘጋጀው መመሪያ እ.ኤ.አ በ2003 የተዘጋጀ እና የኦዲት ሥራው እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያልተከለሰ ሲሆን፤ ይህ የመንገድ ጥገና መመሪያ ለክልል መስተዳደሮች የገጠር መንገዶች ባለስልጣናት እና ለየዲስትሪክቶቹ የተሰራጨበት ሁኔታ ቢኖርም በመመሪያው ላይ የግንዛቤ መስጫ ስልጠና አጥጋቢ በሆነ መልኩ እንዳልተከናወነ በመስክ ስራ ወቅት ከተሰበሰበ መረጃ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

26. የመንገድ ጥገና መመሪያው በየጊዜው አለመከለሱ የሚከናወኑት የመንገድ ጥገናዎች አሁን ካለው የመንገድ ጥገና መሳሪያዎች የቴክኖሎጂ እድገት ጋር ተጣጥሞ እንዳይሔድ የሚያደርግ ሲሆን፣ የመመሪያው ተጠቃሚ ለሆኑት ዲስትሪክቶች ስለአጠቃቀሙ አጥጋቢ ስልጠና እንዲያገኙ አለመደረጉ መመሪያውን በአግባቡ ስራ ላይ በማዋሉ ረገድ ብቃት እንዳይኖራቸው ያደርጋል፡፡

## በባለስልጣኑ የሚተዳደሩ መንገዶች ታሪክ (Road History) በተመለከተ

27. በባለስልጣኑ ሥር የሚተዳደሩ መንገዶች ከመጀመሪያ ግንባታቸው ጀምሮ በየጊዜው የተደረገላቸውን የጥገና ሂደት ታሪክ (Road History) ለአጠቃቀም በሚያመች እና ግልጽ በሆነ ሁኔታ በመረጃ ቋት ሊያዝ ይገባል፡፡

28. በናሙና በተመረጡ በደብረማርቆስ፣ በጎንደር እና በድሬዳዋ ዲስትሪክቶች በተደረገ የመስክ ጉብኝት ከተሰበሰቡ መረጃዎች በየጊዜው ለመንገዶች የተደረጉ የጥገና ሥራዎች በየወሩ፤ በየሩብ ዓመቱ እና በዓመታዊ ሪፖርቶች ውስጥ ተካተው ሪፖርት የሚቀርብበት ሁኔታ ቢኖርም ባለሥልጣኑ ለሚያስተዳድራቸው

መንገዶች ከመጀመሪያ ግንባታቸው ጀምሮ አጠቃላይ ታሪካቸውን የሚያወሳ የመረጃ ቋት (Road History) የማይያዝላቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

29. ባለስልጣን መ/ቤቱ የመንገዶችን ታሪክ በመመዝገብ መረጃ የሚያዝበት የአሰራር ሥርዓት የነበረ ቢሆንም የተዘረጋው የአሠራር ሥርዓት በአሁኑ ወቅት ባለሥልጣን መ/ቤቱ እያስተዳደረ ካለው እና እየጨመረ ካለው የመንገድ አውታር ለማሠራት የማያስችል በመሆኑ ሊቀጥል አለመቻሉን እና አዲስ የመንገድ አስተዳደር (pavement management) ማጠናከሪያ ጥናት ከዓለም ባንክ በተገኘ ድጋፍ በማስቀረጽ ወደ ትግበራ ሊገባ በዝግጅት ላይ መሆኑን ከሚመለከታቸው የባለሥልጣኑ የሥራ ኃላፊ ገልጸ ለመረዳት ተችሏል፡፡

30. መንገዶች ከተገነቡበት ወቅት ጀምሮ ስለመንገዶቹ አጠቃላይ ታሪክና (Road History) ተዛማጅ መረጃዎችን የሚያሳይ የመረጃ ቋት አለመዘጋጀቱ በቀጣይ መንገዶቹን በሚመለከት ለሚከናወኑ ተግባራት አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎች ለማግኘት ስለማያስችል መንገዶቹን ለመጠገንም ሆነ አጠቃላይ ጥበቃ በማድረጉ ሂደት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡

## የመንገድ ጥገና እቅድ ዝግጅትን በተመለከተ

31. የመንገድ ጥገና ከመከናወኑ አስቀድሞ የጥገና ዕቅድ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ የመንገድ ጥገና እቅድ በሚዘጋጅበት ጊዜ ደግሞ የመንገዱን የመጀመሪያ ፕላን፣ ከዚህ ቀደም በመንገዱ ላይ የተካሄዱ የጥገና ሥራዎች እና በእነዚህ ጥገናዎች ወቅት የተገኙ ግኝቶች ወዘተ… ታሳቢ ማድረግ አለበት፡፡

32. የሚያዘጋጁት የመንገድ ጥገና እቅዶች የወቅቱን የመንገዶቹን አገልግሎት ባገናዘበ እና ደረጃን መሠረት ባደረገ መልኩ እንደሆነ እና ለጥገና ከሚመደበው በጀት ዝቅተኛነት የተነሳ የሚከናወነው የጥገና ሥራ በዕቅዱ መሠረት እንዳልሆነ በኦዲት ወቅት ከተለያዩ ዲስትሪክቶች በተገኙ መረጃዎች ላይ የተቀመጠ መሆኑን በመስክ ጉብኝት ወቅት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

33. በእኛ አስተያየት ባለሥልጣኑ የሚያስተዳድራቸው መንገዶች ታሪክ በማይያዝበት ሁኔታ የመንገዶች ጥገና እቅድ የሚዘጋጀው የመንገዱ የመጀመሪያ ፕላን ከዚህ ቀደም በመንገዱ ላይ የተካሄዱ የጥገና ሥራዎችና በእነዚህ ጥገናዎች ወቅት የተገኙ ግኝቶችን ታሳቢ ባደረገ ሁኔታ ነው ለማለት አያስችልም፡፡

## ለመንገድ ጥገና ተግባር የሚውል ፋይናንስ አሰባሰብን በተመለከተ

34. የመንገድ ጥገና ሥራውን በአግባቡ ለማከናወን የሚያስችል ብቃት ያለው የፋይናንሲንግ (የገንዘብ አሰባሰብ ) ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

35. የመንገዶች ፈንድ ጽ/ቤት የዛሬ 12 ዓመት በተቀመጠው ተመን መሠረት ከዘይትና ከቅባት በሊትር 10 ሳንቲም፣ ከነዳጅ ላይ ከተጣለ ታሪፍ ደግሞ በሊትር .2% እየተሰበሰበ የቆየ ሲሆን፣ ከገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በደብዳቤ ቁጥር ታክ/ቀ/5/381 በታዘዘው መሠረት ከሚያዚያ 2003 ጀምሮ በአጠቃላይ ከነዳጅ በወር ብር 107 ሚሊዮን በዓመት ደግሞ 1.3 ቢሊየን በነዳጅ ድርጅት ተሰብስቦ ለመንገዶች ፈንድ ጽ/ቤት ይተላለፋል፡፡ በተጨማሪም ድንበር አቋርጠው ወደ ሀገር ውስጥ ከሚገቡ ተሽከርካሪዎች በትራዚት 15 ዶላር ገቢ የሚሆን ሲሆን፣ በዚህ መንገድ በጽ/ቤቱ ከሚሰበሰበው ገቢ ውስጥ 65 በመቶው የባለስልጣን መ/ቤቱ ለሚያከናውነው የመንገድ ጥገና ሥራ የሚመደብ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

36. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በ2002 በጀት ዓመት ለተለያዩ የመንገድ ጥገና ሥራዎች ብር 650 ሚሊየን ከመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት ተመድቦ በበጀት ዓመቱ ለታቀደ የመንገድ ግንባታ ሊበቃ ስላልቻለ ተጨማሪ ብር 436.2 ሚሊየን ቢጠየቅም ሊፈቀድ የቻለው ብር 159.0 ሚሊየን ብቻ መሆኑ ለመንገድ ጥገና የሚጠየቀው እና የሚፈቀደው የገንዘብ መጠን ምን ያህል ልዩነት እንዳለው ይጠቁማል፡፡ በመሆኑም ለመንገድ ጥገና በሚሰበሰበው ገንዘብ እና ለጥገና በሚያስፈልገው የገንዘብ መጠን መካከል የጎላ ክፍተት እየታየ ይገኛል፡፡ በአሁኑ ሰዓት ባለስልጣኑ የሚያስተዳድረው የመንገድ አውታር (network) መጠን በ10 በመቶ እያደገ እና የጥገና ወጪም እየጨመረ በሄደበት ሁኔታ በየዓመቱ በመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት የሚሰበስበው ገንዘብ ለመንገዶች ጥገና ከሚያስፈልገው ጋር ሲወዳደር ከ60% በታች መሆኑን ጥናቶች ያሳያሉ፡፡

37. በእኛ እምነት ይህ ክፍተት እየሰፋ ለመምጣቱ አስተዋጽኦ ካደረጉ ሁኔታዎች አንዱ ለዚህ ተግባር ሊሆኑ የሚችሉ አግባብነት ያላቸው የገቢ ምንጮች ተለይተው ገቢ እንዲያመነጩ አለመደረጉ ነው፡፡ ከተፈቀደ የክብደት መጠን በላይ ጭነት ተሸክመው የሚገኙት ተሽከርካሪዎች ላይ የሚጣለው ቅጣት ገቢ የመሰብሰብ ኃላፊነት የፈንድ ጽ/ቤቱ ቢሆንም ይህ ቅጣት ገቢ የሚደረገው የሚዛን ጣቢያው ለሚገኝበት ክልል ገንዘብና ኢኮኖሚ ቢሮ መሆኑን ለመረዳት

ተችሏል። ከባለሥልጣኑ በተገኘው መረጃ መሠረት ባለፉት ሶስት የበጀት ዓመታት ማለትም በ2000 ዓ.ም ብር 0.98 ሚሊየን፣ በ2001 ዓ.ም ብር 1.83 ሚሊየን እንዲሁም በ2002 ዓ.ም ብር 4.44 ሚሊየን በድምሩ ብር 7.25 ሚሊየን ከቅጣት መሰብሰቡን ለማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን፣ በመስክ ጉብኝት ወቅት በአሠራሩ ላይ ከተመለከትነው ክፍተተ አንጻር ተገቢው የቁጥጥር እና የክትትል ሥርዓት ቢዘረጋ ከዚህ የተሻለ ገቢ ሊገኝ እንደሚችል ግምት አለን።

38. ስለ ጉዳዩ የመንገዶች ፈንድ ጽ/ቤት ኃላፊ ተጠይቀው ከነዳጅ እና ቅባቶች ጋር በተያያዘ የሚሰበሰበው ገንዘብ በትክክል ገቢ የሚሆንበት ሥርዓት ቢኖርም ጽ/ቤቱ በነዳጅ ላይ ከተጣለ ታሪፍ፣ ከዘይት እና ከቅባት እንዲሁም ድንበር አቋርጠው ከሚገቡ ተሽከርካሪዎች ብቻ ገቢ የሚሰበሰብ መሆኑና ከተፈቀደው ልክ በላይ በጫኑ ተሽከርካሪዎች ላይ የሚጣል ቅጣት፣ ከተሽከርካሪ ቦሎ ሽያጭና ከሀገር ውስጥ የመንገድ ተጠቃሚዎች ፣ ከመንጃ ፈቃድ ዕድሳት ወዘተ የሚሰበሰቡ ገቢዎች አለመካተታቸው ለመንገድ ጥገና የሚሆን የገንዘብ ምንጮች ውስን እንዲሆኑ ማደረጉን እና ጉዳዩን ለማስተካከል ጥናት እየተከናወነ መሆኑን ገልጸዋል።

39. በመሆኑም ባለስልጣኑ የሚያስተዳድረው የመንገድ አውታር (network) መጠን ባገናዘበ ሁኔታ ለመንገድ ጥገና የሚሆን ገቢ ለማሰባሰብ የሚቻልበት ሁኔታ ባለመፈጠሩ በተገቢው ጥራት እና ደረጃ መንገዶች እንዳይጠገኑ፤ በወቅቱ ካልተጠገኑም ከዘገየ በኂላ መንገዶቹን መልሶ ለመገንባት ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅበት ሁኔታ እየተፈጠረ እና የመንገድ ተጠቃሚዎችም የተሻለ አገልግሎት እንዳያገኙ እያደረገ ይገኛል።

## ለመንገዶቹ ወጥ እና ተከታታይነት ያለው ጥበቃ እና ጥገና የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ

40. የመንገዶች ግንባታ እንደተጠናቀቀ ለመንገዶቹ አስፈላጊው ወጥነት እና ተከታታይነት ያለው ጥበቃ እና ጥገና ሊደረግላቸው የሚቻልበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል።

41. በመስክ ከሰበሰብናቸው መረጃዎች ለመረዳት እንደተቻለው ያለው የመንገድ አውታር ሽፋን የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ የሆኑት ዲስትሪክቶች ካላቸው የሠራተኛ ብዛት እና ከሚመደበው በጀት ጋር የማይጣጣም መሆኑ፤ የጎንደር ዲስትሪክት የሚያስተዳደረው 1619 ኪ.ሜ የመንገድ አውታር ሽፋን ሲሆን፣ የተፈቀዱለት የሰባት መሀንዲሶች የሥራ መደቦች ቢሆኑም፣ በመስክ ጉብኝት ወቅት በተገኘው

መረጃ መሠረት ሁለት መሀንዲሶችና አንድ ሱፐርቫይዘር ብቻ በሥራ ላይ እንደነበሩ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በመንገዶች ላይ ለሚደርስ ጉዳት በወቅቱ እርምጃ የማይወሰድ መሆኑ (ፎቶ 1) ከአካባቢው መስተዳደር ጋር ተቀናጅቶ የሚሠራበት ሁኔታ አጥጋቢ አለመሆኑን እና በተለይም ለመንገድ ጥገና የሚያስፈልጉ ግብአቶችን ከአካባቢው ለማግኘት እና የመንገድ ዳር ይዞታዎችን ለማስጠበቅ በሚደረጉ ሂደቶች ላይ የጎላ ችግር መታየቱ ፎቶ 2፣6 እና 7፤) እንዲሁም በመንገድ ዳር ሀብቶች (ምልክቶች) ላይ ከፍተኛ ስርቆት እየተፈጸመ መሆኑን (ፎቶ 3)፤ ለመንገድ ዳር ቦዮች እና ፍሳሽ ማስተላለፊያዎች ወቅታዊ እንንክብካቤ አለመደረጉ (ፎቶ፣4)፡፡ በዚህም የተነሳ በአሁኑ ወቅት እየተከናወነ ያለው የመንገዶች ጥገና እና እንክብካቤ ሥራ በቂ እንዳልሆነ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡



ፎቶ 1፤ በደብረማርቆስ ዲስትሪክት ወይንማ መንደር በመሬት መንሸራተት ምክንያት የተበላሸው መንገድ ተገቢው ወቅታዊ ጥገና ያልተደረገበት ሁኔታ



ፎቶ 2፤ በድሬዳዋ ዲስትሪክት በአደሌ- ግራዋ የመንገድ ፕሮጀክተ የባለሥልጣኑ ይዞታ እና ለመንገድ ጥገና የሚውል ግብአት የሚገኝበት ቦታ በአካባቢው ኗሪዎች ሠፈራ እና መንደር ስለተሠራበት እና የግል ይዞታችን ነው በሚል ለመንገድ ግብአት የሆነውን ኮረት ለማግኘት አልተቻለም፤



**ፎቶ 3፤ በመተማ መስመር ስርቆት የተፈጸመበት የመንገድ ዳር መከላከያ።**



**ፎቶ 4፤ የፍሳሽ ማስወገጃ ቦዮች ተገቢው ክትትል ስላልተደረገላቸው ተደፈኑበት ሁኔታ**



**ፎቶ 5፤** በድሬዳዋ ዲስትሪክት በአደሌ ግራዋ መንገድ ላይ ኅብረተሰቡ የመስኖ ውኃ ለማስተላለፍ መንገዱን በተለያዩ ቦታዎች ላይ በዚህ መልክ የሚሰነጥቅበት ሁኔታ ይታያል፤

42. በመንገዶች ላይ ጉዳት ሲደርስ በፍጥነት ጥገና አለመደረጉ፤ በአካባቢው እና በመንገድ ተጠቃሚው ህብረተሰብ ዘንድ ስለ መንገድ አጠቃቀም እና አጠባበቅ ያለው ግንዛቤ አናሳ በመሆኑ ተቀናጅቶ ለመሥራት እንዳይቻል እና ለመንገዶች የሚደረገው ጥገና በተሻለ ብቃት እና ደረጃ በወቅቱ እንዳይከናወን እያደረገ ይገኛል፡፡

## ከሚመለከታቸው በባለድርሻ አካላት ጋር የመንገድ ጥገና ክንውን ምክክርን በተመለከተ

43. የመንገድ ጥገና ክንውን ሂደትን ለመገምገም እና አግባብነት ያላቸውን ማስተካከያዎች ለማድረግ እንዲቻል ባለስልጣኑ ከሚመለከታቸው የባለድርሻ አካላት ጋር በመንገድ ጥገና የሥራ ሂደት ዙሪያ ለመመካከር የሚችልበት የውይይት መድረክ እንደ አስፈላጊነቱ ቢያንስ በዓመት አንዴ ሊያመቻች ይገባል፡፡

44. ባለስልጣኑ ከሚመለከታቸው የባለድርሻ አካላት ጋር በመንገድ ጥገና የሥራ ሂደት ዙሪያ ለመመካከር የሚችልበት የውይይት መድረክ ቢኖርም ሁሉንም የባለድርሻ አካላት ባሳተፈ መልኩ አለመሆኑን በመስክ ስራ ወቅት ከተሰበሰበ መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በዚህም ምክንያት በተለይ በወረዳ እና በቀበሌ ደረጃ በሚገኙ አካላት የሚደረገው ትብብር ዝቅተኛ እንዲሆን ከማድረጉም በላይ የመንገዶች ጥገና ለማከናወን የሚያገለግሉ ግብአቶችን ከአካባቢው ለማግኘት የሚቻልባቸው እና ባለሥልጣኑ ለረጅም ጊዜ ሲጠቀምባቸው የነበሩ ካሳ የከፈለባቸው ቦታዎችን (quary sites) የአካባቢው ማኅበረሰብ ይዞታዬ ናቸው በሚል፤ በተመሳሳይም በመንገዶች ዳር እና ዳር እንደአስፈላጊነቱ የንድፍ (design) ጥናቱ መሠረት በመንገዱ ይዞታነት ሊከለሉ እና ሊከበሩ ሲገባ በተለይ በትናንሽ ከተሞች እና የገጠር አካባቢዎች እነዚህ ይዞታዎች ያልተከበሩበት እና እስከ መንገዶቹ ጥግ ድረስ ቤቶች እና ልዩ ልዩ ግንባታዎች የተከናወኑበት ሁኔታ እንደሚታይ ለማረጋገጥ ተችሏል (ፎቶ 6-7)፡፡ መፍትሄ እንዲሰጡ የሚጠበቅባቸው የአካባቢው መስተዳድር አካላትም ችግር የሚፈጥሩ ግለሰቦችን የሚደግፉበት ሁኔታ በተደጋጋሚ እንደሚታይ የባለስጣኑ የሥራ ኃላፊዎች እና የድሬዳዋ መስተዳደር መንገዶች ባለሥልጣን ሥራ አስኪያጅ ገልጸዋል፡፡





ፎቶ 6-7፤ በአዲስ አበባ ድሬዳዋ መንገድ በሂርና ከተማ የመንገዶች ዳር እና ዳር ይዞታዎች (right off way) ያልተከበሩበት እና እስከ ዋናው መንገድ ጠርዝ ድረስ ግንባታዎች የተገነቡበት ሁኔታን የሚያሳይ፤

45. ሁኔታውን አስመልክቶ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን የመንገድ ሀብት አስተዳደር ም/ዳይሬክተር ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ ባለሥልጣኑ ለመንገድ ሥራ የሚጠቀምባቸውን ግብዓቶች በነፃ የመጠቀም መብት እንዳለው፤ ሆኖም እነዚህ ግብአቶች ከሚገኙባቸው ቦታዎች ላይ ለተነሱ የህብረተሰብ ክፍሎች የካሣ ክፍያ የተከፈላቸው ቢሆንም በተደጋጋሚ ተመልሰው የሚሰፍሩበት ሁኔታ እንደሚታይ፤ ይህንንም አስመልክቶ ከየዲስትሪክቶች በመጣ ደብዳቤ ችግሩን ለመቅረፍ እንዲቻል ለክልል ፕሬዘዳንት ጽ/ቤቶች የማሳወቅ ሥራ የተሠራ ቢሆንም ችግሮቹ እስከአሁን እንዳልተቀረፉ የገለጹ ሲሆን፣ ወደፊት በባለሥልጣኑ ሥር ያሉ ሁሉም ዲስትሪክቶች የመንገድ ይዞታ እና መብትን ለማስከበር ከወረዳና ከዞን ጋር በመነጋገር ችግሮቹ የሚቀረፉበትን መንገዶችን ማመቻቸት እንዳለባቸው እና በቅድሚያ ለመንገድ ግንባታም ሆነ ለጥገና የሚውሉ ግብዓቶች ያሉበት ቦታዎች (quarry sites) በአካባቢው

ኅብረተሰብ እየተፈጠሩ ያሉ የሠፈራ እና የይዞታ ጥያቄ ችግሮች ከተቀረፉ በኃላ ወደ መንገዶች ይዞታ ማስከበር (right of way) ሥራ እንደሚገባ አስረድተዋል፡፡

46. ባለስልጣኑ ሰፊውን ኅብረተሰብ እና በየደረጃው የሚገኙ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት ባሳተፈ ሁኔታ ቋሚ እና ወጥ የሆነ የውይይት መድረክ አለማዘጋጀቱ በመንገድ ጥገና ዙሪያ የሚነሱ ችግሮች በአፋጣኝ እልባት ሳይገኝላቸው ችግሮቹ እየተስፋፉ የሚሄዱበት ሁኔታ እንዲፈጠሩ ያደርጋል፡፡ ይህ በመሆኑም በመንገዶች ላይ የሚደርሱ ጉዳቶች በመቀነሱ ረገድ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ድርሻውን እንዳይወጣ፤ በቀላሉ ለመከላከል የሚቻሉ ጉዳቶችን ለመከላከል እንዳይቻል እና ለመንገድ ጥገና የሚወጣው ወጪ ከአቅም በላይ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

## ለመንገድ ጥገና የሚውሉ ግብዓቶችን የጥራት ደረጃ ማረጋገጥን በተመለከተ

47. አንድ መንገድ ከመጠገኑ በፊት በተቋራጩ ለጥገና የሚውሉ ግብዓቶች የጥራት ደረጃ ማረጋገጫ በአማካሪ ድርጅቶች ሊሰጥ ይገባል፡፡

48. ከባለስልጣን መ/ቤት ጋር ውል ገብተው በየዲስትሪክቶቹ የመንገድ ጥገና ፕሮጀክቶች ክንውንን ለመከታተል የሚመደቡት አማካሪዎች በፕሮጀክት ቦታ ላይ በመገኘት ለመንገድ ጥገና የሚያስፈልጉ ግብአቶች ላይ ተገቢውን የጥራት ክትትል የሚያደርጉበት ሁኔታ አለመኖሩን በመስክ ካየናቸው የተለያዩ ዲስትሪክቶች ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

49. በእንዲህ አይነት ግብዓት በሚከናወኑ የመንገድ ጥገና ሥራዎች ላይ የጥራት ማነስ እየታየ ይገኛል (ፎቶ 8 እና 9)፡፡ በመሆኑም መንግስት ካለው ውስን በጀት ላይ እየመደበ የሚጠገኑት መንገዶች ማገልገል ያለባቸውን የአገልግሎት ዘመን ሳይሞሉ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለመልሶ ጥገና የሚዳረጉበት ሁኔታ የሚፈጥር እና በአጠቃላይ አማካሪዎቹ በየወቅቱ በመስክ ስራ ላይ በመገኘት የተቋራጭ ድርጅቱ ሥራ ላይ ክትትል አለማድረጋቸው ተቋራጭ ድርጅቱ የሚጠቀመው የመንገድ ጥገና ግብዓት ጥራቱን የጠበቀ እንዳይሆን መንገድ ይከፍታል፡፡

ፎቶ 8፤ በቡሬ ስክሽን በመስክ ስራው ላይ አማካሪው ድርጅት ሳይኖር በዲስትሪክቱ ምህንድስና መምሪያ በኩል ለመንገድ ጥገና ስራው እየተጫነ ያለው ሳር ያለበት የመንገድ ጥገና ግብዓት የተያዘበት ሁኔታ



ፎቶ 9፤ በዚሁ ሴክሽን ለመንገድ ጥገና የዋለውን ከሳር ጋር የተቀላቀለ የመንገድ ጥገና ግብዓት ምክንያት የተበላሸ መንገድ



## የመንገድ ጥገና ሥራዎች በሰው ኃይል እና በአነስተኛ የእጅ መሣሪያዎች ማከናወንን በተመለከተ

50. የመንገድ ጥገና ሥራዎች አዋጭነቱ እና ጠቀሜታው ተገናዝቦ በሰው ኃይል እና በአነስተኛ የእጅ መሣሪያዎች ብቻ በየአካባቢው የሚጠገኑበት አሠራር ሊኖር ይገባል፡፡

51. በሰው ኃይል እና በአነስተኛ የእጅ መሣሪያዎች የመንገድ ጥገና ሥራ የሚከናወንበት ሁኔታ በጅምር ደረጃ ያለ ቢሆንም ተጠናክሮ በስፋት የተሄደበት ሁኔታ አይታይም፡፡ ለመጥቀስ ያህልም በ2002 በጀት ዓመት በሰው ኃይል ለሚደረግ የመደበኛ መንገድ ጥገና 2.07 ሚሊየን ብር በጀት የተያዘ ቢሆንም ብር

1.5 ሚሊየን (74.4%) ለዚሁ ተግባር የዋለ መሆኑን፤ ከዚህ ውስጥ ለሻሸመኔ ዲስትሪክት 0.6 ሚሊየን ብር በጀት ቢያዝም ሥራ ላይ አልዋለም፡፡ እንዲሁም ላለፉት ሁለት በጀት ዓመታት (2002-2003) በድሬደዋ ዲስትሪክት በኩል በሰው ኃይል እና በአነስተኛ የእጅ መሳሪያ የታገዘ የመንገድ ጥገና ለማከናወን ቢታቀድም ተግባራዊ አልሆነም፡፡ በዚህም የተነሳ በአብዛኛው መንገዶቹ ከፍተኛ ወጪ በሚያስወጣው በማሽነሪ በታገዘ የመንገድ ጥገና ስልት እንዲጠገኑ ሲያደርግ መቆየቱን በመስክ ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለመገንዘብ ተችሏል፣፡፡

52. በተጨማሪም ይህን ሥራ እንዲያከናውኑ በጨረታ የተመረጡ ተቋራጮች ሥራቸውን በጨረታ መዘግየት የተነሳ በጊዜ እና በወቅቱ የማይጀምሩበት ሁኔታ መኖሩ፤ በአማራ ክልል በደብረማርቆስ ዲስትሪክት ስር የሚገኘውን አዴት-ባህርዳር 45 ኪ.ሜ የሚሸፍነው መንገድ ጥገና ጨረታው የወጣው በጥቅምት 2003 ዓ.ም አካባቢ እንደነበር እና ጨረታውን ያሸነፈው ተቋራጭ ተረክቦ መጠገን የጀመረው በመስከረም 2004 ዓ.ም መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በዚህም የተነሳ መንገዶቹ ወቅቱን ጠብቀው ባለመጠገናቸው በዮች ተቦርቡረው፣ ተሸርሽረው እና ተደፍነው ፍሳሽ ባግባቡ ማስተላለፍ ባለመቻላቸው መንገዱ የተሰራበትን አፈር በመሸርሸር ለከፍተኛ ጉዳት መጋለጡን ለማየት ተችሏል (ፎቶ 10-12)፡፡



ፎቶ 10፤ ከባ/ዳር - አዴት የፍሳሽ ማስወገጃያው (ቦይ) በዓፈር የተደፈነ ድልድይ



ፎቶ 11፤ ባ/ዳር - አዴት መስመር በአግባቡ የፍሳሽ ማውረጃ ባለመዘጋጀቱ ፍሳሽ መንገዱን ያበላሸበት ሁኔታ



ፎቶ 12፤ በድሬደዋ መስመር የፍሳሽ ማስወገጃ ቦዮች አስፈላጊው እንክብካቤ ስላልተደረገላቸው በአፈር ተደፍነው አፈሩ በመንገዱ ላይ የፈሰሰበት ሁኔታ



ፎቶ 13፤ በድሬደዋ መስመር የፍሳሽ ማስወገጃ ቦዮች አስፈላጊው እንክብካቤ ስላልተደረገላቸው በአፈር ተደፍነው አፈሩ በመንገዱ ላይ የፈሰሰበት ሁኔታ

53. ስለ ጉዳዩ የባለስልጣኑ የመንገድ ሀብት ም/ዋና ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የመንገድ ጥገናን በሰው ኃይል ማሠራቱ የጥገና ወጪ መቀነስ ከማስቻሉም ባሻገር መንገዶች በወቅቱ እንዲጠገኑ እና ለአካባቢው ኅብረተሰብም የሥራ ዕድል እንዲፈጠርለት በማድረግ ድህነትን ለመቀነስም ከፍተኛ አስተዋጾ እንደሚኖረው፤ ይህንንም አሠራር ባለስልጣኑ ትኩረት ሰጥቶት እያከናወነ እንደሆነና ከበጀቱ ከ20-30 በመቶ የሚሆነውን ስራ በሰው ኃይል የጥገና ዘዴ እያከናወነ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

54. ነገር ግን ኃላፊው ሆኖም የተወሰኑ ተግባራቶች በጅምር ደረጃ መታየታቸው ጥሩ ነው ቢያሰኝም በዚህ መልኩ በየአካባቢው የሚጠገኑበት አሠራር በበቂ እና በተጠናከረ ሁኔታ እየተከናወነ ባለመሆኑ ከላይ የተገለጹት ዕድሎችን ለመጠቀም እንዳይቻል አድርጓል፡፡

## ለሚከሰቱ የጥገና መጓተት እና ጥራት ጉድለት ተጠያቂነትን በተመለከተ

55. አማካሪ እና ተቋራጭ ድርጅቶች ውል ገብተው በሚሰሩበት የመንገድ ጥገና ሥራ ላይ ለሚደርስ ጉድለት ተጠያቂ የሚሆኑበት የአሠራር ሥርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊሆን ይገባል፡፡

56. አማካሪም ሆኑ የተቋራጭ ድርጅቶች በመንገድ ጥገና ወቅት ለሚፈጽሙት የጥራት ማነስና የጊዜ ማራዘም ተጠያቂ የሚሆኑበት ሁኔታዎች በሚገቡት ውል ላይ በዝርዝር የተቀመጡ ቢሆንም በውሉ ላይ የተቀመጡ የቅጣትና የካሳ ግዴታዎች በአግባቡና በወቅቱ ተግባራዊ የሚደረጉበት ሁኔታ አለመኖሩን በናሙና ከታዩት የባለሥልጣኑ ዲስትሪክቶች የሥራ ኃለፊዎች ገለጻ ለመረዳት ተችሏል፡፡

57. በሌላ በኩል ደግሞ የስራ ተቋራጮች እና አማካሪ ድርጅቶች በስሩት በሚያጋጥማቸው የባለሙያ ፍልሰት ማለትም ባለሙያዎቹ የጀመሩትን ሥራ ሳያጠናቅቁ በሚለቁበት ወቅት በመንገዶች ጥገና ሂደት ላይ የሚደርሰውን መጓተት ለማቃለል ባለሙያዎቹ የጀመሩትን ሥራ ለማጠናቀቅ ግዴታ የሚገቡበት ሁኔታ የሚፈጠርበትን ሁኔታ ለማመቻቸት በባለስልጣኑ የተጀመረው ጥረት ተጠናክሮ እንዲቀጥል የሚደረግበት ሁኔታ ትኩረት ቢሰጠው የተሻለ መሆኑ በናሙና በታዩ አማካሪ ድርጅቶች ተገልጿል፡፡

58. ስለጉዳዩ የመንገድ ሀብት ማኔጅመንት ም/ ዋና ዳይሬክተር ተጠይቀው እስካሁን ባለው አሰራር ተቋራጭ መንገዱን ጠግኖ ሲያስረክብ ለተወሰነ ጊዜ (defect liability) በውሉ ላይ የተቀመጠ በመሆኑ በዚህ ጊዜ ውስጥ ለሚያደርሰው ጉዳት ኃላፊነቱ የተቋራጩ መሆኑን የገለጹ ቢሆንም ተግባራዊ መሆኑን በተመለከተ የሰጡት ምላሽ የለም፡፡

59. የአማካሪ ድርጅቶችም ሆነ የተቋራጭ ድርጅቶች በመንገድ ጥገና ወቅት ለሚያደርሱት የሥራ ግድፈት ውል ከማቋረጥ ውጪ ለተከሰተው ጉድለት ተጠያቂ የሚሆኑበት ሁኔታ ተግባራዊ አለመደረጉ በመንገድ ጥገና ክንውኑ ላይ ተጠያቂነት እንዳይኖር ያደርጋል፡፡ እንዲሁም የሥራ ተቋራጮችም ሆነ የአማካሪ

ድርጅት ሠራተኞች የጀመሩትን የመንገድ ጥገና ሥራ ሳያጠናቅቁ እና ስራው ያለበትን ደረጃ ሪፖርት ሳያደርጉ የሚለቁበት ሁኔታ መኖሩ የመንገድ ጥገና ሥራው በጥራት፤ በታቀደለት ጊዜ እና በተመደበለት በጀት እንዳይጠናቀቅ ያደርገዋል፡፡

## ከተፈቀደው ክብደት በላይ የጫኑ ሹፌሮች የተቀጡበት የመረጃ አያያዝን በተመለከተ

60. መንገዶች ከሚሸከሙት አቅም በላይ በከባድ ተሽከርካሪዎች ላይ ጭነው የሚያሽከረክሩ ሹፌሮች የተቀጡበት መረጃ የሚያሳይ የመረጃ ቋት ሊዘጋጅ ይገባል፡፡

61. በመስክ ጉብኝት በናሙን በታዩት ሦስት የከባድ ሚዛን ጣቢያዎች ከተገኙ መረጃዎች ከተፈቀደው የጭነት መጠን በላይ የጫኑ ሹፌሮች የተቀጡበትን መረጃ አያያዝ በተመለከተ የክብደት መጠን መቆጣጠሪያ ቅጽ፣ መዝገብ እንዲሁም ለወርሀዊ ሪፖርት ማቅረቢያ የሚያገለግሉ የተለያዩ ቅጾችን የሚጠቀሙ ቢሆንም በነዚህ የመቆጣጠሪያ ጣቢያዎች መረጃዎችን በተፈለጉ ጊዜ በቀላሉ ለማግኘት የሚያስችል የተደራጀ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት አለመኖሩን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የባለሥልጣኑ የተሽከርካሪዎች ክብደት እና መጠን ቡድን መሪ ሁኔታውን አስምልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ ትርፍ የጫኑ አሽከርካሪዎች የተቀጡበት መረጃ የሚያዝበት የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ያለ ቢሆንም የሚዛን ጣቢያዎች ባለባቸው የቁሳቁስ እጥረት በመረጃ አያያዙ ላይ ክፍተት እንደሚታይ እና ይህን ችግር ለመቅረፍ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

62. በየመቆጣጠሪያ ጣቢያዎቹ በተለያየ ጊዜ በተደጋጋሚ ከልክ በላይ ጭነት ጭነው የተቀጡ ሹፌሮችን በቀላሉ ለመለየት ባለመቻሉ የጥፋት ድግግሞሹን ግምት ውስጥ በማስገባት ተመጣጣኝ እና አስተማሪ ቅጣት እንዳይጣልባቸው እና በዚህ ረገድ በመንገድ ላይ እየደረሰ ያለውን ጉዳት ለመቀነስ ያላስቻለ ሲሆን ሁኔታውን በመቆጣጠሩ ሂደት ላይ ብልሹ አሠራር እንዲፈጠር በር ይከፍታል፡፡

## የከባድ ተሽከርካሪዎች ክብደት ቁጥጥር የሚያደርጉ ባለሙያዎች የስነምግባር ደንብን በተመለከተ

63. በባለስልጣኑ ስር በሚገኙ የከባድ ተሽከርካሪዎች ክብደት ቁጥጥር የሚያደርጉ ባለሞያዎች የሚተዳደሩበት የስነምግባር ደንብ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

64. በናሙና ከተመረጡ የክብደት መጠን ቁጥጥር ጣቢያዎች ከተሰበሰቡ መረጃዎች የባለሥልጣኑን የህብረት ስምምነት መሠረት በማድረግ አንድ ሠራተኛ ሲያጠፋ ሊቀጣ የሚገባውን ከመቅጣት በዘለለ ልዩ ትኩረት ለሚያስፈልጋቸው የሥራ መደቦች የሥራውን ባህሪ ባገናዘበ መልኩ የተዘጋጀና ተግባራዊ የሆነ የሥነ ምግባር ደንብ አለመኖሩን፤ ሚዛን ጣቢያዎቹ በተሟላ እና በበቂ የሰው ኃይል አለመደራጀታቸው እንዲሁም አሁን በሥራ ላይ ያለው ሚዛን ካለው የትራፊክ ፍሰት መጠን ጋር የማይጣጣም በመሆኑ በፍጥነት ለማስተናገድ ባለመቻሉ ለተገልጋዮች መሰላቸት እና ለስነ ምግባር ጉድለት ክፍተት የሚፈጥር መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ የባለሥልጣኑ የተሽከርካሪዎች ክብደት እና መጠን ቡድን መሪ ሁኔታውን አስምልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ ለሚዛን ጣቢያ ሠራተኞች ተብሎ የተዘጋጀ የሥነ ምግባር መተዳደሪያ ደንብ የሌለ ቢሆንም በቦታው ላይ ለተመደቡ ሠራተኞች የሥነ ምግባር ሥልጠና የሚሠጥበት ሁኔታ እንዳለ ገልጸዋል፡፡

65. ለሚዛን ተቆጣጣሪ ባለሞያዎች የሚሆን የሥነ ምግባር መተዳደሪያ ደንብ አለመኖሩ፤ ጣቢያዎቹ በበቂ የሰው ኃይል አለመደራጀታቸው እና የትራፊክ ፍሰቱን ለማስተናገድ የሚችል ሚዛን አለመኖሩ ባለሞያዎችን ለአልባሌ እና ለብልሹ አሰራር እንዲጋለጡ ሊያደርግ የሚችል ከመሆኑም በላይ ተገልጋዮች በመሰላቸት ደንብ እና ህግን ሳይጠብቁ እንዲያልፉ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ከተፈቀደው ክብደት በላይ ጭነው በሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች ላይ ተመጣጣኝ ቅጣት የሚጣል ስለመሆኑ

66. ከተፈቀደው ክብደት በላይ ጭነው ለሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች በተጓዙባቸው መንገዶቹ ላይ ከመነሻ እስከ መድረሻቸው ላደረሱት ጉዳት ተገቢውን ቅጣት ሊከፍሉ የሚችሉበት ሥርዓት ሊኖር እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

67. ከተፈቀደላቸው ክብደት በላይ ጭነው የተጓዙበትን ርቀት እና በትርፍ የተጫነውን ክብደት መጠን ያገናዘበ ቅጣት ሊጣል የሚችልበት የአሰራር ስርዓት ባለመኖሩ ተመሳሳይ ለሆኑ ጥፋቶች የተለያየ የቅጣት ውሳኔ የሚሰጥበት ሁኔታ

እንዳለ፤ የሚጣለው ቅጣትና በመንገዱ ላይ የሚደርሰው ጉዳት የማይመጣጠን እና አጥፊዎቹን ከጥፋታቸው እንዲታረሙ የማያደርግ መሆኑ በናሙና በመለየት ከታዩ የሚዛን ጣቢያዎች ከተሰበሰበ መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ  በሀገሪቱ መግቢያ ድንበሮች ላይ የሚዛን ጣቢያዎች ባለመኖራቸው ቁጥጥር የሚደረገው እነዚህ ትርፍ የጫኑ ተሽከርካሪዎች ከድንበር ጀምሮ ረጅም መንገድ ከተጓዙ በኃላ በመሆኑ መንገዶችን ከጉዳት ለመከላከል እንዳልተቻለ እና በመንገዶች ላይ ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰ መሆኑን ከተከለሱ ሰነዶች እና በመስክ ከተሰበሰቡ መረጃዎቸ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ የባለሥልጣኑ የተሽከርካሪዎች ክብደት እና መጠን ቡድን መሪ ሁኔታውን አስምልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ ከላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎች ትክክል መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

68. ከተፈቀደው ልክ በላይ ጭነው የሚያሽከረክሩ ሹፌሮች ካደረሱት ጉዳት አንፃር ተመጣጣኝና አስተማሪ ሊሆን የሚችል ቅጣት እንዲቀጡ ለማድረግ እና የቅጣት አወሳሰን ሂደቱን በተቀላጠፈ ሁኔታ ለማከናወን የሚያስችል የአሠራር ስልት አለመዘርጋቱ  እንዲሁም በድንበር መግቢያ ቦታዎች ላይ የሚዛን ጣቢያዎች አለመተከል ከተፈቀደው በላይ ጭነት የጫኑ ተሽከርካሪዎች በከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ የተሠሩትን መንገዶች በእጅጉ በመጉዳት ያገለግላሉ ተብሎ ከተቀመጠላቸው ጊዜ ቀድመው እንዲበላሹ  በማድረግ በሀገሪቷ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ የጎላ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡

## ለአሽከርካሪዎችና ለሚመለከታቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የመንገድ አያያዝ እና አጠቃቀም ዙሪያ ግንዛቤ መስጠትን በተመለከተ

69. በተሽከርካሪዎች ከልክ በላይ በሆነ ጭነት ምክንያት ለሚከሰቱ የመንገድ ብልሽቶችን አስመልክቶ ለአሽከርካሪዎችና ለሚመለከታቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በየወቅቱ ስልጠና የሚሰጥበት ሁኔታ ሊዘረጋ ይገባል፡፡

70. አሽከርካሪዎችና ባለንብረቶች መንገዶች ሊሸከሙ ከሚችሉት በላይ  መጫን እያስከተለ ያለውን ዘርፈ ብዙ ጉዳት በተመለከተ በቂ ግንዛቤ የሌላቸው እና በተደጋጋሚ ከተፈቀደው ልክ በላይ በመጫን ጥፋቶችን የሚደጋግሙ እና ይህ ድርጊት የሚያስከትለውን ጉዳት ተገንዝበው እንዲታረሙ በቂ የግንዛቤ ስራ አለመሰራቱን  በናሙና በተመረጡ ዲስትሪክቶች በመስክ የስራ ወቅት ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ሁኔታውን አስመልክቶ የተሽከርካሪዎች ክብደት እና መጠን ቡድን መሪ ለሚመለከታቸው የባለ ድርሻ አካላት በየአመቱ የግንዛቤ

ማስጨበጫ ስልጠና የሚሰጥ ቢሆንም በቂ አለመሆኑን እና አጠቃላይ ኅብረተሰቡ መንገዶችን ከመጠበቅ አንጻር ሊጫወት የሚችለውን ሚና ለማስፋት የግንዛቤ መስጫ ስልጠና የሚያገኝበት ሁኔታ መመቻቸት እንዳለበት ገልጸዋል፡፡

71. ለተሽከርካሪ ባለንብረቶች፣ ለአሽከርካሪዎች እና በአጠቃላይ ለኅብረተሰቡ ከመጠን በላይ ክብደት መጫን በመንገዶች ላይ ስለሚያደርሰው ጉዳት በተመለከተ ተመጣጣኝ አና ቀጣይነት ያለው ትምህርት ባለመሰጠቱ ከፍተኛ ወጪ ወጥቶባቸው የተሰሩና የተጠገኑ መንገዶች በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚበላሹበት ሁኔታ እየፈጠረ ይገኛል፡፡

## በመንገድ ጥገና ዘርፍ ሊሰጥ የሚገባ ስልጠናን በተመለከተ

72. በመንገድ ጥገና ዘርፍ የሚገኙ ባለሙያዎች የረዥም እና የአጭር ጊዜ ስልጠናዎች የሚያገኙበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

73. በናሙና ተመርጠው በታዩት አብዛኞቹ ዲስትሪክቶች የቅርብ ጊዜ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ለመጠቀም የሚችል የሰው ኃይል አለመኖሩ፤ ያሉትን ሀብቶች አቀናጅቶ ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማስተዳደር ብቃት ማነስ የሚታዩ ችግሮች ሲሆኑ፣ በመንገድ ጥገና ዘርፍ አግባብነት ያላቸው ሥልጠናዎች የሚሰጧቸው ቢሆንም በተፈለገው አይነት፣ መጠን እና ደረጃ አለመሆናቸውን እና ቀጣይነታቸው ላይ ስጋት እንዳላቸው የሚመለከታቸው የዲስትሪክቶቹ የሥራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

74. በመንገድ ጥገና ዙሪያ በሁሉም ባለድርሻዎች በኩል የልምድ የማነስ ሁኔታ የሚታይ በመሆኑ በዚህ ዙሪያ የተለያዩ ሀገራት ተሞክሮዎችን እንዲሁም ለመንገድ ጥገና የሚሆኑ ሶፍትዌሮችና ከሥራው ጋር ተያያዥ የሆኑ ሥልጠናዎችን በቀላሉ ለማግኘት የሚችሉበት ሁኔታ ቢመቻች በመንገድ ጥገና ሥራው ላይ የተሻለ ውጤት ለመሳየት አስተዋጽኦው የጎላ መሆኑን መጠይቅ ከቀረበላቸው በማማከር ደረጃ ድርሻ ካላቸው ባለድርሻ አካላት ከተሰበሰበ መረጃ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

75. የመንገድ ጥገና ሂደቱን ጥራት የጠበቀና ውጤታማ ለማድረግ በመንገድ ጥገናው ዘርፍ የተሠማራውን የሰው ኃይል ልምድ ለማጎልበት እና ከአዳዲስ ቴክኖሎጂዎችና የምርምር ውጤቶች ጋር ያለውን ግንዛቤ ወቅታዊ ለማድረግ በባለስልጣኑ የተጀመሩ ጅምር ስራዎች ቢኖሩም አጥጋቢ እና አሁን ካለው ፍላጎት ጋር በአይነት፣ በመጠን እና ቀጣይነት ባለው ሁኔታ እንዲከናወን ጥረት

ካልተደረገ ብቃት ያለው የሰው ኃይል በዘርፉ ቀጣይነት ባለው መልኩ ለማግኘት አያስችልም፡፡

76. ስለ ጉዳዩ የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የመንገድ ሀብት ማኔጅመንት ም/ዋና ዳይሬክተር በሰጡት ምላሽ በመንገድ ጥገና ዘርፍ ለሚገኙ ባለሙያዎች የአጭር ጊዜ ስልጠናዎች በተለያዩ አጋጣሚዎች በራስ ኃይልም ሆነ በውጪ ባለሙያዎች እንደሚሰጡ፤ በተለይ የድልድይ ጥገና ላይ በተጠናከረ መልኩ ስልጠናዎች ሲሰጡ በሰው ኃይል የመንገድ ጥገና አሠራር ላይ የተሰጡ ተከታታይ ስልጠናዎች መኖራቸውን ገልፀዋል፡፡

## የመንገድ ጥገና የአፈፃፀም ጥራት አመላካቾችን (performance indicators) ተግባራዊ ማድረግን በተመለከተ

77. የመንገድ ጥገና የአፈፃፀም ጥራት አመላካቾች (performance indicators) በግልጽ ተጠንተው ሊቀመጡ እና ኮንትራክተሮች እነዚህን ጥራት አመላካቾች ተከትለው ሊሠሩ ይገባል፡፡

78. በናሙና ከታዩ ዲስትሪክቶች ደብረማርቆስ እና ጎንደር የመንገድ ጥገና ስራው የመንገድ ጥገና የአፈፃፀም ጥራት አመላካቾችን መሠረት በማድረግ እና በመከተል እየተሠራ አለመሆኑን፤ ነገር ግን ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሚሰጠው የሥራ ትዕዛዝ መሠረት የሚሰራበት ሁኔታ መኖሩን፤ የድሬዳዋ ዲስትሪክት ምህንድስና መምሪያ ተወካይ ደግሞ ለጥያቄው ምላሽ ለመስጠት እንደማይችሉ ገልጸዋል፡፡

79. የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የመንገድ ሀብት ማኔጅመንት ም/ዋና ዳይሬክተር ስለ ጉዳዩ በሰጡት ምላሽ መንገዶች የሚፈልጉትን የጥገና ስራ በተፈለገው የጥገና ጥራት ደረጃ እና ጊዜ ማካሄድ መቻል ዋነኛ ጉዳይ ቢሆንም የመንገዶች ጥገና የአፈጻጸም ጥራት አመላካቾችን ለመጠቀም የሚያስችል ሙሉ በሙሉ የተመቻቸ ሁኔታዎች እንደሌለ፤ ከነዚህ መካከል ለመንገድ ጥገናው የሚመደበው በጀት መንገዶቹን በተፈለገው ደረጃ ለመጠገን የማያስችል መሆኑ፤ ለጥገና በእቅድ ከተያዘው ውጪ ተጨማሪ ሥራዎች በሥራ ሂደት የሚታዩ በመሆኑ እና የጥገና ዳሰሳ ጥናቱ ከተጠና በኃላ ወደ ስራው ሲገባ በሂደት የሚከሰተው የዋጋ ልዩነቶች መኖር፤ እንዲሁም ጊዜው የሚጠይቀውና ለመንገድ ጥገና የሚያስፈልጉ ዘመናዊ መሳሪያዎች ባለመኖራቸው የተነሳ የአፈፃፀም ጥራት

አመላካቾችን (performance indicators) ተከትሎ ለመስራት አዳጋች እንዳደረገው ገልጸዋል፡፡

80. በማከልም ለመንገዶች የሚፈልገውን ጥገና በተገቢው ጥራት እና ጊዜ ለማከናወን በቂ በጀት እንደሚያስፈልግ፤ ባለሥልጣኑ ባለው የሰው ኃይልና በጀት ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባቸውን የመንገድ ጥገና ሥራዎች በመለየት በተቀመጡ መስፈርቶች መሠረት የጥገና ሥራዎችን በመሥራት ላይ እንደሆነ፤ ወደፊት የመንገድ ጥገና የአፈፃፀም ጥራት አመላካቾችን (performance indicators) ተከትሎ ለመሥራት እንዲቻል ጥናቱ በማለቅ ላይ በመሆኑ ወደ ትግበራ ሲገባ የመንገዶችን የጉዳት ደረጃ በተሻለ ሁኔታ በማወዳደር እና በመለየት የጥገናው ሥራ ሊከናወን የሚቻልበትን ሁኔታ እንደሚያመቻች፤ ከዚህ በተጨማሪም በቅርቡ ለመጀመር የታሰበው በውጤት ላይ የተመሰረተ የመንገድ ጥገና ኮንትራት (out put and performance based contract) ሲተገበር የመንገድ ጥገና የአፈፃፀም ጥራት አመላካቾችን ለመተግበር እንደሚቻል እና ችግር ይፈታል የሚል እምነት እንዳላቸው ገልፀዋል፡፡

81. የመንገድ ጥገና ሥርዓት ዋና ዓላማ የመንገድ ኃብትን ለረጅም ዓመታት በተቀመጠለት መስፈርት መሰረት በአግባቡ መጠገን እና ማስተዳደር ሲሆን ከሁለት ዓመታት በፊት በባለሥልጣኑ በተጠናው የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት ላይ በተቀመጠው መሠረት እስካሁን ተግባራዊ አለመደረጉ እና ኮንትራክተሮች የመንገድ ጥገና የአፈፃፀም ጥራት አመላካቾች ተከትለው ባለመስራታቸው የመንገድ ደረጃን በጊዜ፤ በገንዘብ፤ በጥራት እና በብዛት እንዳይጠበቅ ስለሚያደርግ የመንገድ ጥገና ስራዎች ከተጠበቀው የጥራት ደረጃ በታች እንዲጠናቀቁ ያደርጋል፡፡

## የመንገድ ጠርዝ/ትከሻ (road shoulder) ደህንነት መጠበቅን በተመለከተ

82. የመንገድ ጠርዞች (road shoulders) እንዳይጎዱ እና የዋናው የመንገድ ደህንነት ለመጠበቅ እንዲቻል ከፍተኛ ክብደት የጫኑ ተሽከርካሪዎች የማቆሚያ ቦታ እንደአስፈላጊነቱ በየተወሰነ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ (ROAD SIDE STATION) ሊዘጋጅላቸው ይገባል፡፡

83. በናሙና ከታዩ ደብረማርቆስ፤ጎንደር እና ድሬዳዋ ዲስትሪክቶች መካከል ደብረማርቆስ እና ጎንደር የክብደት መጫኛና ማውረጃ በአንዳንድ ከተሞች መግቢያ ላይ ያሉ ሲሆን ከሚሰጡት ጥቅም እና ከአስፈላጊነታቸው አንጻር

የመንገድ ዳር ማረፊያ ቦታዎች በቂ አለመሆናቸውን፣ በድሬዳዋ ዲስትሪክት በመንገዱ ላይ ከፍተኛ ክብደት የጫኑ ተሽከርካሪዎች የሚጠቀሙ ቢሆንም በአብዛኛው በገደላማ አካባቢ ላይ የሚያልፍ በመሆኑ እና የመንገድ ዳር ማረፊያ ቦታዎች ለመገንባት የማያመች መሆኑን ሁኔታውን አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ ከሰጡት ምላሽ እንዲሁም በዚህ ዲስትሪክት ያለውን መንገድ ሁኔታ በመመልከት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

84. የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የመንገድ ሀብት ማኔጅመንት ም/ዋና ዳይሬክተር ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የመንገድ ዳር ማረፊያ ቦታዎች መጀመሪያውኑ በዲዛይኑ ውስጥ አለመካተት አንዱ ችግር መሆኑንና ለመንገዶች መበላሸትም የራሱን የሆነ ተጽዕኖ እንደፈጠረ፤ ይህንንም በመገንዘብ ባለስልጣን መ/ቤት የትራፊክ ፍሰት በሚበዛባቸው ለመጥቀስ በሚሌ እና አዳይቱ አካባቢ ትላልቅ የጭነት መኪኖች ስለሚቆሙ የመንገድ ዳር ማረፊያ ቦታዎች (ROAD SIDE STATION) ለመስራት ጥናቱ ተጠናቆ ለመተግበር በሂደት ላይ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

85. በዋና ዋና መንገዶች ላይ ከፍተኛ ክብደት የጫኑ አሽከርካሪዎች የቴክኒክ ችግር ሲያጋጥማቸው የመኪኖችን ደህንነት ለማረጋገጥ እና ለተለያየ ጉዳዮች በመንገድ ዳር ለመቆም ይገደዳሉ፡፡ ይህም ውስን የሆነውን የመንገድ ስፋት በማጣበብ ለትራፊክ መጨናነቅ እና ለአደጋዎች መባባስ ዋነኛ ምክንያት ይሆናል፡፡ እንዲሁም ማረፊያ ቦታዎች ለማግኘት በማይቻልባቸው መሰመሮች ላይ አሽከርካሪዎች ለረጅም ሰዓታት ስለሚያሽከረክሩ በመዳከም ለአደጋ የሚጋለጡበት ሁኔታ ይከሰታል፡፡

## በመንገድ ጥገና ሥራዎች ላይ ወጥነትና ተከታታይነት ያለው የጥራት ቁጥጥር ኦዲት መደረጉን በተመለከተ

86. በመንገድ ጥገና ሥራዎች ላይ ወጥነትና ተከታታይነት ያለው የጥራት ቁጥጥር ኦዲት ገለልተኛ በሆነ አካል የሚደረግበት ስርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

87. በናሙና ካየናቸው ሶስት ዲስትሪክቶች ከተሰበሰበ መረጃ መንገዶች ጥገና ከተደረገላቸው በኃላ የጥራት ቁጥጥር ኦዲት ገለልተኛ በሆነ አካል የማይደረግ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የመንገድ ሀብት ማኔጅመንት ም/ዋና ዳይሬክተር ሁኔታውን አስመልክቶ በሰጡት ምላሽ በወቅታዊ ጥገና ሥራዎች ላይ የጥገና ክትትል እና የጥራት ቁጥጥር ተግባር በአማካሪ

መሐንዲሶች እንዲሁም የመደበኛ ጥገና በዲስትሪክት ምህንድስና መምሪያዎች በኩል እየተከናወነ እንደሚገኝ፤ በሌላም በኩል በመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት ከዚህ በፊት ሁለት ጊዜ የክዋኔ ኦዲት የተካሄደ እና በቅርብም ከአዴግራት ዲስትሪክት እና ከመቀሌ ዩኒቨርስቲ ጋር በመተባበር የጥራት ቁጥጥር ኦዲት መከናወኑን፤ ሆኖም ቀጣይነት ባለው መልኩ በሁሉም የመንገድጥገናዎቸ ላይ እንደማይከናወን ገልፀዋል፡፡

88. ተከታታይነት ያለው የጥራት ቁጥጥር ኦዲት የመንገድ ጥገናዎች በአግባቡ ለመከናወናቸው ገለልተኛ አስተያየት ለመስጠት የሚከናወን ተግባር ሲሆን ፣ ይህ የቁጥጥር ኦዲት መንገዶች ጥገና ከተደረገላቸው በኋላ አለመከናወኑ ለመንገድ ጥገና የሚሰጠው ትኩረት አናሳ መሆኑን ያሳያል፡፡ በመሆኑም በመንገዶች ጥገና ላይ የሚታዩ ጉድለቶችን በማጣራት እና ገለልተኛ አስተያየት በማቅረብ በሚመለከተው አካል የማስተካከያ የእርምት እርምጃ እንዳይወሰድ ያደርጋል፡፡

## መንገዶች ሊሰጡ የሚጠበቅባቸውን ወቅታዊ አገልግሎት ባገናዘበ መልኩ የመንገዶች ጥገና የሚከናወን መሆኑን በተመለከተ

89. መንገዶች በሚፈለገው ሁኔታ አገልግሎት እንዲሰጡ የወቅቱን የመንገዶቹ አገልግሎት ባገናዘበ መልኩ እና ደረጃቸውን መሰረት በማድረግ ጥገና የሚያገኙበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

90. የመንገዱን ነባራዊ እና ወቅታዊ ሁኔታ በማገናዘብ እንደ መንገዱ ደረጃ እና የጥገና ዓይነት በየዓመቱ ጥገና የሚያስፈልጋቸውን መንገዶች በመለየት የጥገና ዕቅድ እንደሚዘጋጅ፤ ከፍተኛ የትራፊክ ፍሰት ላለባቸው እና ከፍተኛ ጉዳት ለደረሰባቸው መንገዶች ቅድሚያ የሚሰጥ መሆኑ፤ ሆኖም ለመንገድ ጥገና በዕቅድ የሚያዘው እና የተጠየቀው በጀት ስለማይመደብ መንገዶቹ በተፈለገው እና የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት ለመስጠት በሚያስችላቸው ደረጃ የማይጠገኑ መሆኑ በናሙና ተመርጠው የታዩ የባለሥልጣኑ ዲስትሪክት የሥራ ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

91. የትራፊክ ፍሰት እንቅስቃሴ እና ሌሎች በወቅቱ ሊታዩ የሚችሉ ሁኔታዎች በመንገድ ጥገና ዕቅዶች ውስጥ ለማካተት የሚቻል ቢሆንም የመንገዶቹ ታሪክ እና ሌሎች ተያያዥ መረጃዎች ተጠናቅረው ለአጠቃቀም በሚያመች መልኩ በማይያዙበት ሁኔታ የጥገና ዕቅዱን በተሟላ መልኩ ለማዘጋጀት የሚያስችል

መረጃ ለማግኘት ያስችላል የሚል ዕምነት አይኖርም፡፡ በመሆኑም የመንገድ ጥገናዎች አቅም በፈቀደው እና በተመደበው በጀት እንኳ በሚፈለገው ደረጃ ለመጠገን ስለማያስችል ተጠገኑ የተባሉ መንገዶች ያገለግላሉ ተብሎ ከታሰበው እድሜ በታች በአጭር ጊዜ ውስጥ ለብልሽት የሚዳረጉበት እና በቀጣይ የሚጠይቀው የመንገድ ጥገና ወጪም እየናረ እንዲሄድ ያደርጋል፡፡

## የመንገድ ጥገና ከመከናወኑ በፊት የአካባቢ እና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ መደረጉን በተመለከተ

92. የመንገድ ጥገና ከመከናወኑ በፊት የአካባቢ እና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ቀደም ሲል በመንገዱ ግንባታ ወቅት የተጠና መሆኑ ሊረጋገጥ እና ከሌለ ጥናቱ ተከናውኖ ሊቀርብ፤ በተጠናው ጥናት መሠረት የጥገና ፕሮጀክቱ ተግባራዊ ለመሆኑ ክትትል ሊደረግ እና በመንገድ ጥገና ሥራ ወቅት የሚወጡ አላስፈላጊ አካባቢን ሊበክሉ የሚችሉ ዝቃጮች እና ሌሎች ጎጂ ሁኔታዎች በአግባቡ የሚወገዱበት ሥርዓት ሊዘረጋ፤በመጨረሻም ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ የፕሮጀክቱ ክንውን እና መንገዱም አገልግሎት በሚሰጥበት ወቅት በአካባቢ ላይ ሊያደርስ የሚችለውን ጎጂ ተጽዕኖ ለመቀነስ የተቀመጡ ስልቶች እና አማራጮች ተግባራዊ ስለመደረጋቸው ኦዲት ተደርጎ ሪፖርት እንደ አስፈላጊነቱ በየጊዜው ሊቀርብ ይገባል፡፡

93. ለመስክ ሥራ በሄድንባቸው ዲስትሪክቶች የመንገዶች ግንባታ ከመከናወኑ በፊት ሊደርስ የሚችለው የአካባቢና ማህበራዊ የተጽዕኖ ግምገማ በዶክመንት ደረጃ የሚዘጋጅና ያለ ቢሆንም ይህን ጥናት መሠረት በማድረግ ሊደርሱ የሚችሉ ተፅዕኖዎችን ለመከላከል እቅድ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ አለመደረጉን እና መንገዶቹ ከተገነቡ በኋላ በቀጣይ በሚከናወኑ የጥገና ሥራዎች ወቅት በአካባቢ ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ጉዳቶች ትኩረት እንዳልተሰጣቸው እና በመንገዶች ላይ እና ዳርቻዎች ላይ ጉዳት እየደረሰ መሆኑን ካገኘናቸው መረጃዎች ለመገንዘብ ተችሏል (ፎቶ፤ 14-16)፡፡ ስለሁኔታው የሚመለከታቸው የባለስልጣኑ የሥራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በጎላ መልኩ አካባቢውንና ማኅበረሰቡን የሚጎዳ የመንገድ ጥገና ስራ ይከናወናል ተብሎ ስለማይታሰብ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ በዕቅድ እንደማይካተት እንዲሁም መንገዶች አገልግሎት በሚሰጡበት ወቅት በአካባቢ ላይ ሊያደርስ የሚችለውን ተፅዕኖ ለመከላከል የአካባቢ ጥበቃ እቅድ (Enviromental Management plan) የሚዘጋጅ ባይሆንም መንገዱ አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜ በአካባቢ ላይ ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስ

ከአካባቢው ሕብረተሰብ ጋር በመወያየት ወቅታዊ መፍትሄ እንደሚሰጥ ገልጸዋል፡፡

94. በአካባቢና ማኅበረሰቡ ላይ ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት ግምት ገብቶ ለመንገድ ጥገና ተግባራት የአካባቢ እና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት አለመከናወኑ እና ይህን ጥናት መሠረት በማድረግ የአካባቢ ጥበቃ እቅድ (Enviromental Management plan) ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ባለመደረጉ በመንገድ ጥገና እና ከጥገና በኃላ አገልግሎት በሚሰጡበት ወቅት የሚከሰቱት የአፈር መከላት፣ የሬንጅ ዝቃጭ እና ሌሎች ተረፈ ምርቶች  በአካባቢ ላይ ጉዳት በማድረስ በኅብረተሰቡ  ሕይወት እና ጤና ላይ ችግር ሊያስከትሉ የሚችሉ ቢሆንም እና ይህን ጥናት መሠረት በማድረግ የአካባቢ ጥበቃ እቅድ (Enviromental Management plan) ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ባለመደረጉ በመንገድ ጥገና እና ከጥገና በኃላ አገልግሎት በሚሰጡበት ወቅት የሚከሰቱት የአፈር መከላት፣ የሬንጅ ዝቃጭ እና ሌሎች ተረፈ ምርቶች  በአካባቢ ላይ ጉዳት በማድረስ በኅብረተሰቡ  ሕይወት እና ጤና ላይ ችግር ሊያስከትሉ ይችላሉ




ፎቶ 14፤ በደብረ ማርቆስ ዲስትሪክት የመንገድ ዳር የፍሳሽ ማስወገጃ ቦዮች ከአግባቡ ባለመሠራታቸው እና እንክብካቤ ና ጥገና ባለመደረጉ በአካባቢ ላይ ኣየደረሱ ያሉ ጉዳቶችን የሚያሳዩ

ፎቶ 15-16፤ በደብረ ማርቆስ ዲስትሪክት የመንገድ ዳር የፍሳሽ ማስወገጃ ቦዮች ባለመሠራታቸው ከአካባቢው ገበሬዎች ማሳ ላይ እና ከመንገዶች ላይ እየደረሱ ያሉ ጉዳቶችን የሚያሳዩ ምስሎች






# ክፍል ሦስት

## መደምደሚያ

95. ባለሥልጣኑ በአሁኑ ወቅት በከፍተኛ መዋለ ንዋይ የሀገሪቱን የመንገድ አውታር ደረጃ እና መጠን ከማሳደግ አኳያ አበረታች ሥራዎችን እየሠራ መሆኑን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን፤ ይህን ተግባር ተከትሎ ላሉት እና በየጊዜው እየጨመረ የመጣውን የመንገድ አውታር በአግባቡ ከመጠበቅ እና ከመጠቀም አንጻር ትኩረት ሊያደርግ ይገባል፡፡

96. መንገዶች ከተገነቡበት ወቅት ጀምሮ ስለመንገዶቹ አጠቃላይ ታሪክና (Road History) ተዛማጅ መረጃዎችን የሚያሳይ የመረጃ ቋት አለመዘጋጀቱ፤ ለሚዛን ተቆጣጣሪ ባለሞያዎች የሚሆን የስነምግባር ደንብ አለመኖሩ እና ጣቢያዎቹ በበቂ የሰው ኃይል አለመደራጀታቸው እንዲሁም በእነዚህ የሚዛን ጣቢያዎች የትራፊክ ፍሰትን በብቃት ማስተናገድ አለመቻሉ፤ በተጨማሪም በተለያየ ጊዜ በተደጋጋሚ ከልክ በላይ ጭነት ጭነው ያሽከረከሩ እና የተቀጡ ሹፌሮችን በቀላሉ በመለየት የሚያስችል እና የቅጣት አወሳሰን ሂደቱን በተቀላጠፈ ሁኔታ ለማከናወን የሚያስችል የአሠራር ስልት አለመዘርጋቱ፤ በመግቢያ ድንበሮች ላይ እንደ አስፈላጊነቱ የሚዛን ጣቢዎች እንዲኖሩ አለመደረጉ፤ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ ሁኔታ የመንገድ ጥበቃ እና አጠቃቀምን በተመለከተ የግንዛቤ መፍጠሪያ እና የውይይት መድረክ አለማዘጋጀቱ፤ በዋና ዋና መንገዶች ዳር ከፍተኛ ክብደት ለጫኑ ተሽከርካሪዎች ማቆሚያ አለመዘጋጀቱ በከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ የተሠሩ መንገዶች ላይ ጉዳት እንዲደርስ በማድረግ መንገዶቹ እንዲያገለግሉ ከተያዘላቸው ወቅት አስቀድመው ለከፍተኛ ጉዳት እንዲዳረጉ እያደረገ ይገኛል፡፡

97. የመንገድ ጥገናዎች በአግባቡ ለመከናወናቸው ለማረጋገጥ ተከታታይነት ያለው የጥራት ቁጥጥር ኦዲት አለመከናወኑ፤ በአካባቢና ማኅበረሰቡ ላይ ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት ግምት ውስጥ ገብቶ ለመንገድ ጥገና ተግባራት የአካባቢ እና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናትን መሠረት በማድረግ የአካባቢ ጥበቃ እቅድ (Enviromental Management plan) ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ባለመደረጉ በመንገድ ጥገና እና ከጥገና በኃላ አገልግሎት በሚሰጡበት ወቅት በአካባቢ ላይ ጉዳት በማድረስ በኅብረተሰቡ ሕይወት እና ጤና ላይ ቀላል የማይባል የጽዕኖ

ያደርሳል፡፡ እነዚህን ግድፈቶች ለማስተካከል የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል ተቀምጠዋል፡፡

# የማሻሻያ ሀሳቦች

## ለመንገዶች ጥገና የሚያገለግለው መመሪያ ወቅታዊ መሆኑን እና ግንዛቤን በተመለከተ

98.ባለስልጣን መ/ቤቱ ለመንገዶች ጥገና የሚያገለግለውን መመሪያ ተግባራዊ ከሚያደርጉ ባለድርሻ አካላቶች ጋር በጋራ በመሆንና መመሪያውን ሊከልስ እና ወቅታዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በመንገድ ጥገና ዙሪያ በየወቅቱ የሚወጡትን ቴክኖሎጂዎች ያገናዘበና እና ያካተተ ዕውቀት እንዲኖራቸው በማድረግ የተሻለ እና የተቀላጠፈ የመንገድ ጥገና እንዲከናወን ስለ መንገድ ጥገና መመሪያ አጠቃቀም ለሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት ተከታታይነት እና ወጥነት ያለው ስልጠና የሚሰጥበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

## በባለስልጣኑ የሚተዳደሩ መንገዶች ታሪክ (Road History) በተመለከተ

99.በአንድ መንገድ ላይ በቀጣይ ሊሰሩ የሚችሉ የጥገና ስራዎችን ውጤታማ ለማድረግና የመረጃ ክፍተትን ለመቀነስ የመንገዱን ግንባታ፣ መንገዱ ከተገነባ በኋላ በመንገዱ ላይ ስለተከናወኑ የጥገና ስራዎች እና ሌሎች ተዛማጅ ሁኔታዎች የሚገልጹ መረጃዎች የሚያዝበት የመንገድ ታሪክ ቋት ባለሥልጣኑ ለሚያስተዳድራቸው ሁሉም መንገዶች ሊደራጅ ይገባል፡፡

## የመንገድ ጥገና እቅድ ዝግጅትን በተመለከተ

100. ባለሥልጣኑ የሚያስተዳድራቸው መንገዶችን ታሪክ በአግባቡ መያዙ የመንገድ ጥገና እቅድ በሚዘጋጅበት ወቅት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ማለትም የመጀመሪያ ፕላን፣ ከዚህ ቀደም በመንገዱ ላይ የተካሄዱ የጥገና ሥራዎችና በእነዚህ ጥገናዎች ወቅት የተገኙ እና ተካተው ሊከናወኑ የሚገቡ ነጥቦችን በቀላሉ ለማግኘት የሚረዳ በመሆኑ ትኩረት ሊሰጠው እና እነዚህ መረጃዎች ታሳቢ ተደርገው የመንገዶች ጥገና ዕቅድ የሚዘጋጅበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

## ለመንገድ ጥገና የሚሆን የፋይናንስ አሰባሰብን በተመለከተ

101. ባለስልጣኑ ከመንገዶች ፈንድ ጽ/ቤት እና ከተለያዩ ድጋፍ ሰጪ አካላት ጋር በመተባበር በገቢ አሰባሰቡ ክንውን ላይ የሚታዩ ድክመቶችን ለመለየት የሚደረገው ጥናት ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶት ከነዳጅ፣ ከትርፍ ጭነት፣ ከመንገድ ተጠቃሚ አካላት ከሚሰበሰቡ የተለያዩ ክፍያዎች፣ ከተላላፊ ተሽከርካሪዎች ክፍያ (transit fee) ወዘተ ላይ ተገቢው ታሪፍ የሚጣልበትን እና የመንገድ ፈንድ ገቢው ሊያድግ የሚችልበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡ ከዚህም

ባሻገር ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎችና የምርምር ተቋማት ጋር በመተባበር በአነስተኛ ወጪ የመንገድ ጥገናን ለማከናወን የሚያስችል ስልት ተቀርፆ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

## ለመንገዶቹ ወጥ እና ተከታታይነት ያለው ጥበቃ እና ጥገና የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ

102. መንገዶቹ በወቅቱ መጠገናቸው እና እንክብካቤ ቢደረግላቸው ከማንም በላይ በቅርብ ለሚገኘው የኅብረተሰብ ክፍል ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን እና ባለመጠገናቸውም ተጎጂው ይኸው ኅብረተሰብ እንደሚሆን ለአካባቢው ኅብረተሰብም ሆነ ለባለሥልጣናቱ ግንዛቤ መስጠት እንዲሁም ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በማሳወቅ በመንገድ ጥበቃ እና እንክብካቤ ሥራ ከባለስልጣኑ ጀምሮ እስከ ቀበሌ ድረስ ባሉ አስፈጻሚ አካላት እና የህብረተሰብ ክፍሎች ሊተገበሩት የሚገባቸው ሥራዎች ተለይተው ሁሉንም በየደረጃው የሚገኙ አካላትን ሊገዛ የሚችል የመግባቢያ ሰነድ የሚያዘጋጅበት ሁኔታ ቢፈጠር እየታየ ያለውን የቅንጅት ችግር ለማቃለል አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ለመንገድ ጥገና የሚውሉ ግብዓቶችን የጥራት ደረጃ ማረጋገጥን በተመለከተ

103. ተቋራጭ ድርጅቶች የሚያቀርቡት የመንገድ ጥገና ግብአት ጥራት ያለው እንዲሆን የተሻለ ቁጥጥር ሊደረግ አማካሪዎች የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ የተሻለ ክትትል የሚደረግበት መንገድ እንዲፈጠር ጥረት ሊደረግ ይገባል፡፡

## የመንገድ ጥገና ሥራዎች በሰው ኃይል እና በአነስተኛ የእጅ መሣሪያዎች ማከናወንን በተመለከተ

104. በአነስተኛ የእጅ መሣሪያዎች ብቻ ሊከናወኑ የሚገባቸውን የመንገድ ጥገና ስራዎችን ለይቶ በዚህ መልኩ እንዲከናወኑ ማድረጉ ባለው የበጀት አቅም የተሻለ ሰፊ ሽፋን ያለው የመንገድ ጥገና ስራ ለማከናወን ከመስቻሉም በላይ ለዜጎች ከፍተኛ የሆነ የስራ እድል በተሻለ ሁኔታ ለመፍጠር ያስችላል፡፡ በዚህ ዙሪያ የተወሰኑ ተግባራቶች በጅምር ደረጃ መታየታቸው ጥሩ ቢሆንም በዚህ መልኩ በየአካባቢው የሚጠገኑበት አሠራር በበቂ እና በተጠናከረ ሁኔታ እየተከናወነ ባለመሆኑ ከላይ የተገለጹት ዕድሎችን ለመጠቀም እንዳይቻል አድርጓል፡፡ ባለስልጣኑ በሰው ኃይል እና በአነስተኛ የእጅ መሣሪያዎች የመንገድ አጠጋገንን የሚያስለጥንበት ማስልጠኛ ያለው በመሆኑ ይህንን መልካም አጋጣሚ

በመጠቀም ዘርፉ በሰፊው የሚያጠናክርበት ሁኔታ ቢቀየስ የመንገድ ጥገና ስራ የሚያስፈልገውን ወጪ የሚቀንስ ከመሆኑም ባሻገር አነስተኛ ሀገር በቀል ተቋራጮች እንዲስፋፉ የጎላ አስተዋጽኦ ስለሚኖረው ትኩረት እንዲሰጠው ሊደረግ ይገባል፡፡

## ለሚከሰቱ የጥገና መጓተት እና ጥራት ጉድለት ተጠያቂነትን በተመለከተ

105. የስራ ተቋራጮች እና አማካሪ ድርጅቶች በሚያጋጥማቸው የባለሙያ ፍልሰት ምክንያት በመንገድ ጥገና ስራ ላይ የሚፈጠረውን መጓተት ለመቀነስ ባለሙያዎቹ በተቀጠሩበት ሥራ ላይ ለማገልገል ውል በገቡበትን ወቅት ለማጠናቀቅ ግዴታ ሊገቡ የሚችሉበት እና ይህን ባያሟሉ ተጠያቂ የሚደረጉበት የአሠራር ሥርዓትን በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

## ከተፈቀደው ክብደት በላይ የጫኑ ሹፌሮች የተቀጡበት የመረጃ አያያዝን በተመለከተ

106. መንገዶች ሊሸከሙ ከሚችሉት መጠን በላይ በመጫን ተደጋጋሚ ጥፋት ያጠፉ አሽከርካሪዎችን በቀላሉ በመለየት እርምጃ ለመውሰድ እንዲቻል በሁሉም የሚዛን ጣቢያዎች ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ስርዓትን በመዘርጋት የሚዛን ጣቢያዎችንም ሆነ ከዋናው መ/ቤት ጋር በመረጃ መረብ እንዲገናኙ በማድረግ የመረጃዎችን ስርጭት እና ተደራሽነት ለማሻሻል ጥረት ሊደረግ ይገባል፡፡

## የከባድ ተሽከርካሪዎች ክብደት ቁጥጥር የስነምግባር ደንብን በተመለከተ

107. በሚዛን መቆጣጠሪያ ጣቢያ ላሉ ሠራተኞች ስለ መንገድ ደህንነት እና የአክስል ክብደት መቆጣጠር አስፈላጊነት የስነምግባር ትምህርት ሊሠጥ፤ በቦታው ላይ የሚመደቡ ሠራተኞች ኃላፊነት እና ተጠያቂነት እንዲኖራቸው ለቦታው የስነ ምግባር ደንብ በጥናት በባለሞያዎች ሃሳብ ዳብሮ ሊዘጋጅ እና ተግባራዊ ሊደረግ እንዲሁም የትራፊክ ፍሰቱን ያገናዘበ ሚዛን በየቦታው (በየአካባቢው) እንዲኖር ጥረት ሊደረግ ይገባል፡፡

## ከተፈቀደው ክብደት በላይ ጭነው ለሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች ላደረሱት ጉዳት ተመጣጣኝ ቅጣት መጣልን በተመለከተ

108. ከተፈቀደው የጭነት ልክ በላይ ጭነው በሚጓዙ ተሽከርካሪዎች የተነሳ በመንገዶች ላይ ሊደርስ የሚችለውን ብልሽት ለመቀነስ እንዲቻል በመንገዱ ላይ ከደረሰው ጉዳት መጠን ጋር ተመጣጣኝ እና ወጥ የሆነ የቅጣት መጠን ለመወሰን እንዲሁም የቅጣት ሂደቱ የሚወስደውን ጊዜ ለመቀነስ የሚያስችል ሥርዓት በጥናት ሊዘረጋ በተጨማሪም ከባድ ተሽከርካሪዎች ወደ ሀገሪቱ ድንበር

ሲገቡ ቁጥጥሩን ከመነሻው ለማድረግ እንዲቻል የክብደት መጠን ቁጥጥር ጣቢያዎች ከመግቢያ ድንበሮች ላይ ሊተከሉ የሚችልበት ሁኔታ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

## ከሚመለከታቸው በባለድርሻ አካላት ጋር የመንገድ ጥገና ክንውን ምክክርን በተመለከተ

109. ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ባሳተፈ ሁኔታ በመንገድ ጥገና ዙሪያ ያጋጠሙ ችግሮችና ሊወሰዱ የሚገባቸው የእርምት እርምጃዎችን በተመለከተ የውይይት መድረክ ማዘጋጀቱ ችግሮች ተለይተው ወቅታዊ መፍትሄ እንዲያገኙ በማድረግ የመንገድን ጥገና በወቅቱ ጥራቱን በጠበቀ ሁኔታ ለማከናወን እንዲቻል እና በመንገዶች መልሶ ግንባታ ሊወጣ የሚችለውን ከፍተኛ ወጪ ለመቀነስ የጎላ አስተዋጽኦ ስለሚኖረው ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

## ለአሽከርካሪዎችና ለሚመለከታቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የመንገድ አያያዝ እና አጠቃቀምን በተመለከተ ግንዛቤ መስጠትን በተመለከተ

110. ለከባድ ጭነት አሽከርካሪዎች፣ ለባለንብረቶች፣ ለማህበራት፣ ለአስመጪዎችና ለሚመለከታቸው ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ተሽከርካሪዎች ከተፈቀደ ክብደት በላይ ጭነው በሚጓዙበት ወቅት በከፍተኛ ወጪ የተሰሩት መንገዶች ላይ የሚደርሰው ብልሽት የሚያስከትልውን ዘርፈ ብዙ ጉዳት በማስገንዘብ በመንገዶች ላይ የባለቤትነት መንፈስ እንዲኖራቸው ማድረግ ለመንገዶች ጥበቃና እንክብካቤ አስተዋጾው የጎላ ስለሆነ በተከታታይ እና በተጠናከረ መልኩ በመንገዶች አያያዝና አጠባበቅ ዙሪያ ግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡

## በመንገድ ጥገና ዘርፍ ሊሰጥ የሚገባ ስልጠናን በተመለከተ

111. የቅርብ ጊዜ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ለመጠቀም የሚችል የሰው ኃይል ለማፍራት እና ያሉትን ውስን ሀብቶች አቀናጅቶ ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማስተዳደር እንዲቻል ከሙያው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ባለሙያዎች ከማብቃት አንጻር በባለሥልጣኑ ጥሩ ጅምር ያለ ቢሆንም በተጠናከረ መልኩ ሁሉንም ባለድርሻ አካላት በማካተት የተሻሉ ተሞክሮዎች እና ሌሎች አስፈላጊ ስልጠናዎች በተከታታይነት ሊሰጥ የሚችልበት መድረክ ሊመቻች ይገባል::

**የመንገድ ጥገና የአፈፃፀም ጥራት አመላካቾችን (performance indicators) ተግባራዊ ማድረግን በተመለከተ**

112. ኮንትራክተሮች የመንገድ ጥገና የጥራት አመላካችን ተከትለው ቢሰሩ የመንገድ ጥገናን በጊዜ፣ በገንዘብ፣ በጥራት እና በብዛት እንዲከናወን እና የመንገድ ጥገና አገልግሎት በወቅቱ ለመንገድ ተጠቃሚ እንዲደርስ የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ የኮንትራክተሮች ኃላፊነት እና ተጠያቂነት እንዲጠናከር ያደርጋል፡፡ በመሆኑም ባለሥልጣኑም ከሁለት ዓመት በፊት ባጠናው የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት ላይ ባስቀመጠው የአፈፃፀም ጥራት አመላካቾችን መሠረት ኮንትራክተሮች እንዲሰራ የሚያደርግ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋትና ተግባራዊነቱን ሊከታተል ይገባል፡፡

**የመንገድ ጠርዞች (road shoulders) ደህንነት መጠበቅን በተመለከተ**

113. የመንገድ ዳር ማረፊያ ቦታዎች በመንገድ ግምባታም ሆነ ጥገና ፕላን ውስጥ እንዲካተቱ እና እንዲገነቡ ማድረጉ በመንገዶች ጠርዝ ላይ የሚደርሰውን ጉዳት እና ከጊዜ ወደ ጊዜ በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ የሄደውን የትራፊክ አደጋ ለመቀነስ ስለሚያግዝ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

**በመንገድ ጥገና ሥራዎች ላይ ወጥነትና ተከታታይነት ያለው የጥራት ቁጥጥር ኦዲት መደረጉን በተመለከተ**

114. ባለስልጣን መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው የባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት በተለይ ከመንገዶች ፈንድ ጽ/ቤት ጋር በመተባበር በተከናወኑ የመንገድ ጥገናዎች ላይ ወቅታዊና ተከታታይነት ያለው የጥራት ቁጥጥር ኦዲት ማድረጉ የሚወጣው ወጪ በአግባቡ ለተባለለት አላማ መዋሉና ገልልተኛ በሆነ አካል ማረጋገጥ ከማስቻሉ ባሻገር የመንገድ ጥገና ሥራዎች ጥራታቸውን ጠብቀው እንዲከናወኑ የራሱን አስተዋፅኦ ስለሚኖረው ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

**መንገዶቹ ሊሰጡ የሚጠበቅባቸውን ወቅታዊ አገልግሎት ባገናዘበ መልኩ ጥገና የሚደረግላቸው መሆኑን በተመለከተ**

115. የሚመደበውን ውስን በጀት በአግባቡ በመጠቀም ጥገና የሚደረግላቸው መንገዶች የሚጠበቅባቸውን ወቅታዊ አገልግሎት ሊሰጡ በሚችሉበት ደረጃ እንዲጠገኑ አስተዋጽኦ ስለሚኖረው የመንገዶች ጥገና ዕቅድን ለማቀድ የሚያስፈልጉ በቂ መረጃዎች ሊያዙ እና ሊሟሉ የሚችሉበት ሁኔታ እንዲሁም በመንገዶች ጥገና ላይ በተሰማሩ ተቋራጮች መካከል ጤናማ የውድድር መንፈስ ቀጣይነት ባለው መልኩ ሊፈጠር የሚችልበትን ሁኔታ ለማስፈን ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

## የመንገድ ጥገና ከመከናወኑ በፊት የአካባቢ እና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ መደረጉን በተመለከተ

116. ባለስልጣኑ ለመንገድ ጥገና ዘርፍ ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ የሚሰራበት ሁኔታ ሊመቻችና  በመንገዶች ጥገና ወቅት በአካባቢ ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ጉዳቶችን ግምት ውስጥ በማስገባት  የአካባቢ እና ማህበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት ሊጠና፤ የመንገዶች ጥገና በሚከናወንበትም ሆነ ጥገናው ተጠናቆ አገልግሎት በሚሰጡበት ወቅት ተገቢ ያልሆነ ጉዳት በአካባቢ ላይ እንዳያስከትሉ ክትትል የማድረጊያ እና ችግሮች ሲገኙም በወቅቱ  ለማቃለል የሚያስችል የአካባቢ ጥበቃ እቅድ (Enviromental Management plan)  ሊዘረጋና እንዲሁም ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ የፕሮጀክቱ ክንውኑ በአካባቢ ላይ ሊያደርስ የሚችለውን ጎጂ ተጽዕኖ ለመቀነስ የተቀመጡ ስልቶችን እና አማራጮችን ተግባራዊ ለመደረጋቸው መንገዱም አገልግሎት በሚሰጥበት ወቅት በአካባቢ ላይ ሊደርሱ የሚችሉትን ተጽዕኖዎች ለመቀነስ የሚያስችል እርምጃ እየተወሰደ ለመሆኑ ክትትል የማድረጊያ ሥርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

# አባሪዎች

አባሪ1

## የኦዲት መመዘኛዎች

I. በባለሥልጣኑ የሚከናወኑ የመንገድ ጥገና ተግባራት በቁጠባ (economicaly) እና በብቃት (efficiently) እየተከናወኑ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡

ሀ. የመንገድ ጥገና ሥራን ለማከናወን አግባብነት ያለው የአሠራር ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡

1. ለመንገዶች ጥገና የሚያገለግለው መመሪያ በየጊዜው ያለውን ወቅታዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ሊሻሻል ይገባል:: ከተሻሻለ በኃላ በአግባቡ ሊሰራጭ ይገባል ስለአጠቃቀሙ አስፈላጊው ስልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡
2. የመንገድ ጥገና እቅድ በሚዘጋጅበት ጊዜ የመንገዱ የመጀመሪያ ፕላን ከዚህ ቀደም በመንገዱ ላይ የተካሄዱ የጥገና ሥራዎችና በእነዚህ ጥገናዎች ወቅት የተገኙ ግኝቶች ታሳቢ ማድረግ አለበት፡፡
3. የመንገድ ጥገና ስራ ለማከናወን የሚያስችል ብቃት ያለው የፋይናንሲንግ (የገንዘብ አሰባሰብ ) ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡
4. የመንገዶች ግንባታ እንደተጠናቀቀ ለመንገዶቹ አስፈላጊው ወጥነት እና ተከታታይነት ያለው ጥበቃ እና ጥገና የሚደረግላቸው ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡
5. አንድ መንገድ ከመጠገኑ በፊት በተቋራጩ ለጥገና የሚውሉ ግብዓቶች የጥራት ክትትል ማረጋገጫ በአማካሪ ድርጅቶች ሊሰጥ ይገባል፡፡
6. የመንገድ ጥገና ሥራዎች አዋጭነቱ እና ጠቀሜታው ተገናዝቦ በሰው ኃይል እና በአነስተኛ የእጅ መሣሪያዎች ብቻ በየአካባቢው የሚጠገኑበት አሠራር ሊኖር ይገባል፡፡
7. ለኮንትራክተሮች ለጨረታ የሚቀርበው የመንገዶች ጥገና ዋጋ ወቅታዊ ሁኔታን ባገናዘበ መልኩ ተከልሶ (reasonable price escalation) ሊቀርብ ይገባል፡፡
8. በባለስልጣኑ የሚተዳደሩ መንገዶች ታሪክ (Road History) በየጊዜው የተደረገላቸውን የጥገና ሂደት ለአጠቃቀም በሚያመች እና በግልጽ በሚታይ መልኩ በመረጃ ቋት ሊያዝ ይገባል፡፡
9. አማካሪ እና ተቋራጭ ድርጅቶች ውል ገብተው በሚሰሩበት ሥራ ላይ ለሚደርስ ጉድለት ተጠያቂ የሚሆኑበት የአሠራር ሥርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊሆን ይገባል፡፡
10. መንገዶች ከሚሸከሙት አቅም በላይ በከባድ ተሽከርካሪዎች ላይ ጭነው የሚያሽከረክሩ ሹፌሮች የተቀጡበትን የሚገልጽ የመረጃ ቋት ሊዘጋጅ ይገባል፡፡
11. በባለስልጣኑ ስር በሚገኙ የከባድ ተሽከርካሪዎች ክብደት ቁጥጥር የሚያደርጉ ባለሞያዎች የሚተዳደሩበት የስነምግባር ደንብ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

12. ከተፈቀደው ክብደት በላይ ጭነው ለሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች መንገዶቹ ላይ ከመነሻ እስከ መድረሻ ላደረሱት ጉዳት ተገቢውን ቅጣት ሊከፍሉ የሚችሉበት ሥርዓት ሊኖር እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

**ለ. በሚያከናውነው የመንገድ ጥገና ዙሪያ ከሚመለከታቸው የውስጥ እና የውጭ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እና ቁጠባን መሠረት በማድረግ በብቃት እየተሠራ መሆኑን መገምገም፡፡**

13. በባለሥልጣኑ የሚዘጋጀው የመንገድ ጥገና መመሪያ ከሚመለከታቸው የባለድርሻ አካላት ጋር አስፈላጊው ውይይት ተደርጎና ዳብሮ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡
14. የመንገድ ጥገና ክንውን ሂደትን ለመገምገም እና አግባብነት ያላቸውን ማስተካከያዎች ለማድረግ እንዲቻል ባለስልጣኑ ከሚመለከታቸው የባለድርሻ አካለት ጋር በመንገድ ጥገና የሥራ ሂደት ዙሪያ ለመመካከር የሚችልበት የውይይት መድረክ እንደ አስፈላጊነቱ ቢያንስ በዓመት አንዴ ሊመቻች ይገባል፡፡
15. በተሽከርካሪዎች ከልክ በላይ በሆነ ጭነት ምክንያት ለሚከሰቱ የመንገድ መበላሸቶችን አስመልክቶ ለአሽከርካሪዎችና ለሚመለከታቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በየወቅቱ ስልጠና የሚሰጥት ሁኔታ ሊዘረጋ ይገባል፡፡
16. በመንገድጥገና ዘርፍ ለሚገኙ ባለሙያዎች የረዥም እና የአጭር ጊዜ ስልጠናዎች የሚያገኙበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡
17. በመንገድጥገና ዘርፍ ለሚገኙ ባለሙያዎች የረዥም እና የአጭር ጊዜ ስልጠናዎች የሚያገኙበት ሁኔታሊመቻች ይገባል፡፡

**II. በባለሥልጣኑ የሚከናወኑ የመንገድ ጥገና ሥራዎች የጥራት ደረጃቸውን ጠብቀው ስኬታማ (effective) በሆነ ሁኔታ የሚከናወኑ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡**

18. ለመንገድ ጥገና ዙሪያ ለሚከናወኑ ተግባራት የጥገና የጥራት ደረጃ ሊረጋገጥበት የሚያስችል ወጥ የሆነ የጥራት ማረጋገጫ መመሪያ (GUIDE LINE & PROCEDURE) ሊዘጋጅና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
19. የመንገድ ጥገና የአፈፃፀም ጥራት አመላካቾችን (performance indicators) በግልጽ ተጠንተው ሊቀመጡ እና ኮንትራክተሩ እነዚህን ጥራት አመላካቾች ተከትሎ ሊሠራ ይገባል፡፡
20. የመንገድ ጠርዞች (road shoulders) እንዳይጎዱ እና የዋናው የመንገድ ደህንነት ለመጠበቅ እንዲቻል ከፍተኛ ክብደት የጫኑ ተሽከርካሪዎች የማቆሚያ ቦታ በየተወሰነ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ (ROAD SIDE STATION) ሊዘጋጅላቸው ይገባል፡፡
21. በመንገድ ጥገና ሥራዎች ላይ ወጥነትና ተከታታይነት ያለው የክትትልና የጥራት ቁጥጥር ኦዲት የሚደረግበት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡
22. መንገዶች በሚፈለገው ሁኔታ አገልግሎት እንዲሰጡ የወቅቱን የመንገዶቹ አገልግሎት ባገናዘበ መልኩ እና ደረጃን መሰረት በማድረግ ጥገና የሚያገኙበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

**III. ባለሥልጣኑ የመንገድ ጥገና በሚያከናውንበት ወቅት በአካባቢ ላይ የሚያደርሰውን ተፅእኖ ለመቀነስ ተገቢ እርምጃ የሚወስድ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡**

23. የመንገድ ጥገና ከመከናወኑ በፊት የአካባቢ እና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ሊከናወን እና ሪፖረት ሊቀርብ፤
    - በተጠናው የአካባቢ እና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ መሠረት የጥገና ፕሮጀክቱ ተግባራዊ ለመሆኑ ክትትል ሊደረግ
    - በመጨረሻም ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ የፕሮጀክቱ ክንውኑ በአካባቢ ላይ ሊያደርስ የሚችለውን ጎጂ ተጽዕኖ ለመቀነስ የተቀመጡ ስልቶችን እና አማራጮችን ተግባራዊ ለማድረጉ ኦዲት ተደርጎ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡
24. መንገዶች አገልግሎት በሚሰጡበት ወቅት በአካባቢ ላይ ተገቢ ያልሆነ ጉዳት እንዳያስከትሉ ክትትል የማድረጊያ ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊሆን ይገባል፡፡
25. በመንገድ ጥገና ሥራ ወቅት የሚወጡ አላስፈላጊ አካባቢን ሊበክሉ የሚችሉ ዝቃጮች በአግባቡ የሚወገዱበት ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

# አባሪ 2

## የመንገድ አውታር ዝርጋታ መጠን፤

| ተ.ቁ | መንገዶቹን የሚያስተዳድረው | የርቀት መጠን በኪ.ሜ |
|---|---|---|
| 1 | በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን | 18,188 |
| 2 | የክልል መንገዶች ባለሥልጣን | 21,778 |
| 3 | በወረዳ (ማሕበረሰብ) | 100,384 |
| | በድምሩ | 140,350 |